# ማኅቶት ፤



የደመራ በዓል በተከበረበት ወቅት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

መስከረም ፲፱፻፸፫ ዓ. ም. ቍጥር ፫

www.ethiopianorthodox.org

## ማዕዶት

ማዕዶት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ ከልሳነ ግዕዝ ሲሆን ትርጓሜውም ሽግግር ወይም መሸጋገሪያ ማለት ነው ።

ይህ መጽሔት በዚህ ታዳጊ ዓለምና የሽግግር ወቅት ውስጥ በተሐድሶ ላይ የምትገኘውን ጥንታዊቷንና ታሪካዊቷን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት ፣ ታሪክና ዜና ጠቅላላ ሕልውናዋንና ወቅታዊ እንቅስቃሴዋን ሁሉ የሚገልጽ ስለሆነ ማዕዶት ተብሎ ተሠየመ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ በስብከትና ማስታወቂያ መምሪያ እየተዘጋጀ በየሦስት ወሩ አንድ ጊዜ የሚታተም ፤


አዘጋጅ ፤

ወልደ ሩፋኤል ፈታሒ

የስልክ ቁጥር 110754

የመልእክት ሣጥን ቁጥር 1283


## ማውጫ ፤


| | አርእስት | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩/ | ርእሰ አንቀጽ | ፩ |
| ፪/ | ፪ኛ ዓመት የፓትርያርኩ በዓለ ሢመት | ፫ |
| ፫/ | ፓትርያርኩ በ፪ኛው ዓመት በዓለ ሢመት ያስተላለፉት ቃለ በረከት | ፮ |
| ፬/ | አቶ መርስዔ ኃዘን አበበ የቤተ ክህነቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ያደረጉት ንግግር | ፱ |
| ፭/ | ፓትርያርኩ ለዘመን መለወጫ ያስተላለፉትቃለ በረከት | ፲፪ |
| ፮/ | ዓለም አቀፍ ዜናዎች | ፲፫ |
| ፯/ | የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለመልሶ ማቋቋሚያያ ደረገችው ርዳታ | ፲፭ |
| ፰/ | የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የጀግኖች እምባ ጉብኝት | ፲፭ |
| ፱/ | በሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤና በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ የተደረጉ ሴሚናሮች | ፲፰ |
| ፲/ | መስቀልና ታሪካዊ አመጣጡ | ፳፩ |
| ፲፩/ | ተአምራታዊ ዜናዎች | ፳፪ |
| ፲፪/ | የበዓላትና የአጽዋማት መግለጫ | ፳፬ |


### (ርእሰ አንቀጽ)

# አዲሱን ዐመት ስንቀበል

እንደኢትዮጵያ ዘመን አቈጣጠር የ፲፱፻፸፪ ዓ/ም አሮጌ ዐመት አልፈን የ፲፱፻፸፫ ዓ/ም አዲስ ዐመት ለመቀበል እነሆ በከፍተኛ ዝግጅት ላይ እንገኛለን ፤ በባህላችንና በወጋችን መሠረት እንኳን ለአዲሱ ዐመት አበቃችሁ እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገራችሁ የሚለው አነጋገር ከዘመን መለወጫ ጀምሮ ባሉት ጥቂት ሳምንታት የምንጠቀምበት የተለመደ ዘይቤአችን ነው ። በእነዚህ ሳምንታት ተበድረን ተለቅተን እያሌ የግብዣ ልውውጥ እናደርጋለን ፤ ብዙ የመዝናኛ ሥፍራዎችንም እንጎበኛለን አዳዲስ ልብሶችንም መልበስ እንወዳለን በአጠቃላይ አነጋገር ዐውደ ዐመትና ሌሎችም የበዓላት ቀኖች በመጡ ቍጥር ውስጡን ለቄስ መኾናችንን እኛው ራሳችን እየተገነዘብነው ስንቸገር ያልተቸገርን ፤ ስናጣ ያላጣን ሲከፋን ያልከፋን በመምሰል ያልኖረውን ለመኖርና ያልኾነውን ለመኾን ስንሞክር እንታያለን ።

በተግደርዳሪው ባሕርያችን በመጠኑ መደሰታችንንና በትንሹ ለመለወጥ መሞከራችንን ፈጽመን ልናወግዘው ባይገባንም አንዱ ዘመን አልፎ ሌላው ዘመን በመጣ ቍጥር መንፈሳችን ሊጨነቅበትና ሊጠበብበት የሚገባው ከዚህ በላይ ለምሳሌ ያህል በተጠቀሰው ቌሳቍስ ወይም ኀላፊና ጠፊ ነገር ብቻ መሆን የለበትም አሮጌውን ዐመት አልፈን ዐዲሱን ዐመት ስንቀበል ያለፈውን ዓመት በምን ዓይነት ተግባር እንዳሳለፍነው በትጋት ወይስ በስንፍና በልማት ወይስ በጥፋት ? የሚመጣውንም ዐመት በምን ዓይነት ተግባርለመቀበል እንደተዘጋጀን ማሰብና መገመት ዓይነተኛው ተግባራችን ነው ። ባለፈው ዐመት ባደረግነው ስሕተት የደረሰብን ጉዳትና የኑሮ መቃወስ ቢኖር ያንን በማስታወስ በአዲሱ ዐመት እንዳይደግመን ከስሕተታችን መማር ይገባል ።

ዘመን የሰው ልጆች የሥራ መመዘኛና የሕይወት መለኪያ በመኾኑ አንዱን ትውልድ አሳልፎ ሌላውን ትውልድ ሲተካ የሚኖር በምድር ላይ የሚኖረውን ሕያው ሥነፍጥረት አፈራራቂ ነገር ስለኾነ ማርጀትና መታደስ የሌለበት ሲኾን ሁልጊዜ ለውጥንና መታደስን በሚሹ በሰው ልጆች ባሕርይ እየተወከለ አሮጌ ዓመት አዲስ ዓመት ሲባልመኖሩ የተለመደ ጉዳይ መኾኑ ባይካድም በዘመናት መካከል የምንገኝ የአዳም ዘሮች በሥራ ካልተለወጥንና ካልታደስን በስተቀር ዘመን በመለወጡ ልንለወጥ ፤ አዲስ ዐመትም በመምጣቱ አዲስ ልንኾን አንችልም ። ዘመኑ አዲስ ዘመን ዓመቱም አዲስ ዐመት ሊኾን የሚችለው እኛ በሠራነው አዲስ ሥራና እኛ ባስገኘነው ለውጥ መሆኑን ተገንዝበን ለአዲስ ሥራና ለአዲስ መንፈስ መዘጋጀት አለብን ።

« ጊዜና ውሃ ሙላት ሰውን አይጠብቅም » በተባለው መሠረት ዘመን ወደፊት የመ ገሥገሥ እንጅ ወደኋላ የመመለስ ባሕርይ ስለሌለው እኛ የሰው ልጆች ከዘመን የምንማረው ነገር ቢኖር ወደፊት መራመድንና ወደኋላ አለማለትን ነው ። ከፉም ይኹን ደግጊዜን በየዓመቱ በእንግድነት የምንቀበለው ወደፊት ሲሄድ እንጅ ወደኋላ ሲመለስ ባለመኾኑ ወደፊት መራመድን ከጊዜ ልንማር ይገባናል ፤ በየዘመኑ አዲሱን ዐመት በእንግድነት ስንቀበለው እንደምንኖር ሁሉ ጊዜም እኛን እንዲቀበለን ያስፈልጋል መቸም መች ጊዜ በእኛ ላይ ሲያልፍብን እንዲኖር አያስፈልግም ። እኛ በጊዜ ላይ እንድናልፍበት ያስፈልጋል ። ቀድመነው ልንሄድ ባንችልም እንኳን አብረነው መሮጥ ተገቢያችን ነው ።

አዲሱን ዐመት ስንቀበል አዲስ መንፈስና ኅብረት አዲስ ፍቅርና አዲስ የሥራ ዕቅድ እንዲኖረን ያስፈልጋል ፤ የሰው ልጆችን ሁልጊዜ አዲስ ሲያደርጋቸው የሚኖረው ሁልጊዜ ሕያው የኾነው ሥራቸው እንጅ የዘመናት አዲስነትና የጊዜያት በጊዜያት መፈራረቅ ስለአልኾነ በአዲስ ዐመት በአዲስ መንፈስና በአዲስ የሥራ ዕቅድ የማይዘጋጅ ሰውነት ሁሉ ፤አስተዳደሩን ለማሻሻልና ርምጃውን ለማሳመር የማይጣጣር ድርጅት ሁሉ ነፍስ እንደተለየው ሥጋ የሞተ እንጅ ሕያውነት እንደአለው አካል አይገመትም ይህ እንዳይኾን ባለፈው አሮጌ ዐመት የገጠሙንን መጥፎ ድርጊቶች የመ

www.ethiopianorthodox.org

ማሪያ መጻሕፍት በማድረግ ካለፈው ስሕተት ርቀን ለወደፊቱ በተቀደሰና በነቃ መንፈስ መዘጋጀት ግዴታችን ነው ።

የጨለማው የብርዱና የውሽንፍሩ ወራት ክረምቱ አልፎ የብርሃኑ የአበባውና የፍሬው እንዲሁም የሙቀቱ ወራት በጋው ሊተካ እንደተቃረበ ኹሉ እኛም የአድኃሪነት ጠባያችንን አስወግደን ከተንኰልና ከፋት ርቀን ባለፈው የሠራነውን ልዩ ልዩ ኃጢአት ተገንዝበን በንስሐ በመታደስ አዲሱን ዐመት በተቀደሰ መንፈስ እንድንቀበለው በተለይ ክርስቲያኖች ለኾን ሁሉ የክርስትና ግዴታችን ስለኾነ ዘመናትን ሲያመላልስ ለዘለዓለም ለሚኖር ጌታ አዲስ ዝማሬ ልናቀርብለትና ልንጸልይ ይገባል ሁሉ ነገር ሥምረት ሊኖረው የሚችለውና የሰው ልጆች የወጠኑት ተግባር ሁሉ ፍጻሜ የሚያገኘው የእግዚአብሔር ረድኤት ሲጨመርበት መሆኑን ማመን የክርስትና ዓላማ ነውና ።


---

# ፲ኛ ዓመት የፓትርያርኩ በዓለ ሢመት

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ዐራተኛ ዓ

ስለዚህ ከፍተኛ መንፈሳዊ በዓል ከቤተ ክህነት ጠቃላይ ጽቤት በወጣው መርሐ ግብር (ፕሮግራም

ያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን መገኘት በዓሉን ታላቅ የቤተ ክርስቲያን በዓል መሆ



፲ኛ ዓመት የፓትርያርኩ በዓለ ሢመት

መት የፓትርያርክነት በዓለ ሢመት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በከፍተኛ ድምቀት ተከብሮ ውሏል ።

መሠረት ነሐሴ ፳፱ ቀን ለ፳፫ አጥቢያ የአዲስ አበባ አድባራት ካህናትና ሊቃውንት በመንበረ ፓትር

ኑን የሚያበሥር ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ አድረዋል ።

በዚህ ፣ በዓል ላይ ጥሪ የተደረገላ



www.ethiopianorthodox.org

ቸው የመንግሥት ባለሥልጣናትና የዓለም አቀፍ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንዲሁም የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ዓባላት ና የየድ ርጅቱ ተወካዮች ተገኝተዋል ።

የተውጣጡ ልብሰ ተክህኖና ጥንግ ድርብ የለበሱ መዘምራንና ካህናት ለበዓሉ በተዘጋጀው ሥፍራ ተገ ኝተው የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያር ኩን መምጣት ይጠባበቁ ነበር ፤

ቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ታጅበው ከበዓሉ መከበሪያ ሥፍራ ግሉት ከመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ግር ያም ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ እንደደረሱ ለሦስት ደቂቃ ያህል የደ



በ፪ኛው ዓመት የፓትርያኩ በዓለ ሢመት ካህናትና ወጣት መዘምራን በዝ ማሬ ላይ እንዳሉ ።

እንደበዓሉ አከባበር ፕሮግራም አወጣጥ ከጧቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ሲሆን የአዲስ አበባ አድ ባራት አለቆችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንዲሁም ከየአድባራቱ

በዚሁ ሁኔታ በዐራት ሰዓት ከሩብ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ «ናስ ተበጽእሙ ለእለበአሚን ወረሱተስ ፋሆሙ»የሚለውያሬዳዊ ዜማበመዘ ምራንእየተዘመረላቸው በብፁዓንሊ

ወል ድምፅ ከመሰማቱም በላይ ካህናቱና ዲያቆናቱ «ቡሩክ ዘይመ ጽእ በስመ እግዚአብሔር» የሚለ ውን መዝሙር እየዘመሩ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚያም ሦስት



መዘምራን ከብፁዕ ወቅዱስ ፓትር ያርኩ ፊት ቀርበው ለበዓሉ ተስማ ሚ የሆ ነ ውን ግለት «ኃረየከ እብ ሚ የሆ ነውን ግለት «ኃረየከ እብ ኃረየከ ወልድ ወእግሕፀነከ ኃበ እሙ ኢትዮጵያ ኃረየከ መንፈስ

መምሪያ አማካይነት ከአዲስ አበባ አድባራት የሰንበት ት/ቤቶች የተው ጣጡ ወጣት መዘምራን ልዩ ልዩ ያሬዳዊ ዜማዎችን አሰምተዋል ። ቀጥሎም የተፈቀደላቸው ሊቃው

ሥራ አስኪያጅ ቤተ ክርስቲያን ባለ ፉት ሁለት ዓመታት ስለፈጸሙትው ብሔር አቀፍና ዓለም አቀፍ ርምጃ ወደፊትም ሊሠሩ ስለታቀዱት የተ ስፉ ዕቅዶች በማስመልከት ሰፋ



ብፁዐን ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት በ፪ኛው ዓመት የፓትርያርኩ በዓለ ሢመት በተደረገው ግብዣ ላይ ፤

ቅዱስ ወረሰየከ ሠረገላሁ ትሩፈ ዙሉ ምግባር ተክለ ሃይማኖት መል አከ ዘበምድር»የሚለውን ግሥ ኪቃ ኙና ካህናቱ ግሡን በመቀባበል ካሸበሸቡ በኋላ በወጣቶች ጉዳይ

ንት ከቅዱስ ፓትርያርኩ ዘንድ በየ ተራ እየቀረቡ ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔዎችን አበርክተዋል ከዚህም በማያያዝ አቶ መርስዔ ኃዘን አበበ የጠቅላይቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና

ያለ ንግግር አድርገዋል ።

በመጨረሻም ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርከ ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶ ክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪ ክና ይዞት እንዲሁም ባለፉት ዓመ



www.ethiopianorthodox.org

ታት ስለፈጸመችው ብሔራዊ አገል ግሎት ወደፊትም ስለምትከተለው ዓላማ በመዘርዘር ቃለ በረከት አስ ተላልፈዋል ።

በዐውደ ምሕረቱ የተከናወነው ዝግ ጅት በዚህ ሁኔታ እንደተፈጸመ ከቀኑ በ፯ ሰዓት ተኩል ላይ የጸሎተ ቅዳሴው ሥርዓት በቅዱስነታቸው መሪነት ተጀምሮ ልክበ፰ ሰዓት ተ ኩል ከተከናወነ በኋላ ጠቅላላ የበ ዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

በዚሁ ዕለት ስለበዓሉ ከፍተኛ ነት ለመንግሥት ባለ ሥልጣኖችና ጥሪ ለተደረገላቸው እንግዶች እን ዲሁም ለካህናትና ለሊቃውንት በመንበረ ፓትርያርኩ የስብከተ ወንጌል አዳራሽ የምሳ ግብዣ ተደ ርጓል ።

በዚህም ወቅት አለቃ አያሌው ታምሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ ሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበር በዓሉን በማስ መርከዝ ስለኢትዮጵያ ቤተ ክርስ ቲያን የታሪክና ወደፊት ሊፈጸም ስለ ሚገባው የስብከተ ወንጌል መስ ፋፋትና መጠናከር የሚያመለክት ንግግር አድርገዋል እንዲሁም አቶ መርስኤ ኃዘን አበበየጠቅላይ ቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪ ያጅና ሌሎችም ሊቃውንት መወ ድስ ቅኔዎችን ካበረከቱ በኋላ ብፁዕ አቡነ መቃርዮርስ የጎጃም ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስና የውጭ ግን ኙነት ኃላፊ የበዓሉን ታላቅነትና አስደሳችነት በመግለጽ ጸሎተ ቡራ ኬ ከሰጡ በኋላ የግብዣው ፍጻሜ ሆኗል ።

# ፓትርያርኩ በ፩ኛው ዓመት በዓለ ሢመት ያስተላለፉት ቃለ በረከት ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በ፩ኛው ዓመት በዓለ ሢመተ ፓትርያርክ የሚከተለውን ቃለ በረከት አስተላልፈዋል ። «ኢኩት እግዚአብሔር በእንተ ጸጋሁ እንተ ኢትተረጐም ወትመጽእ አመ ኢተሐዘብዋ» ስለማትመረመር ባላወቋት ዕለት ባልጠረጠሩዋት ሰዓት ስለምትሰጥ ጸጋው እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን ። (፪ ቆሮ ፱ ፣ ፲፭) ።



ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ በ፩ኛው ዓመት በዓለ ሢመተ ፓትርያርክ ቃለ በረከት በሰጡበት ወቅት ፤

በምሥራቁና በምዕራቡ ዓለም ውስጥ ታሪክና ሥርዓት፤ ብሔራዊ ባህልና ልማድ ካሉዋቸው አ ብያተ ክርስቲያናት መካከል አንድዋ የኢ ትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት ። ለዚህ ምስክሮች



እኛ ብቻ አይደለንም ። ዓለም አቀፍ የቤተ ክርስታያን ታሪክም ይመስክ ራል ። የታሪክ ምስክርነትም በሁሉ ዘንድ የታመነ ነው ። ቤተ ክርስቲ ያናችንን ጥንታዊትና ታሪካዊት የሚያሰኛት ረዥም ዘመናትካላቸው አብያተ ክርስቲያናት አንድዋ ሆና መቈጠርዋ ብቻ አይደለም ። በጌታ ችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመሠረተውን በቅዱሳን ሐዋርያት የተሰበከውን በአበው ሊቃውንት የጸናውን ትምህርተ ሃይማኖት ጠብቃ ቅዱሳት መጻሕ ፍትን ጠንቅቃ ሳትከልስ ሳታፋልስ ይዛ እስካሁን መቆየትዋም ጥንታዊ ትና ታሪካዊት ሊያሰኛት ችሏል ። ለምሳሌ ቅዱስ ጳውሎስና ሐዋር ያው ይሁዳ በየመልእክታቸው የጠ ቀሱት መጽሐፈ ሄኖክ በዓለም ሁሉ ሊገኝባልቻለ ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ መገኘቱ የታሪክ መድበልነትዋንና የ ቅ ር ሳ ቅ ር ስ ጠባቂነትዋን አረጋግጦአል ።

ይህ ብቻም አይደለም የክርስትና ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ሁሉ ሲሰበክ ብዙ ሀገሮች የሐዋር ያቶቻቸውን ደም አፍስሰዋል ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ግን የማንም ሐዋርያ ደም ሳይፈስባት ተመሥርታለች። በውስጥና በውጭ ታሪክ የታወቀው በ፫ኛው ምእት ዓመት አጋማሽ ላይ በፈቃደ እግ ዚአብሔር የተላከላትን ሐዋርያ ፍሬምናጦስን በሰላም ተቀብላ የክ ርስቶስን ወንጌል በሰላም ተማረች እንጂ አልተቃወመችም ። ይልቁ ንም ሢመት መንፈሳዊን ወደ ሚያ ገኝበት ሀገር ልካ ጳጳስ እንዲሆንላት አድርጋለች ። በትምህርቱና በስብ ከቱም ስለ ሰላም የምትሰበ ክና ለሰው ልጆች ብርሃን የሆነች ወንጌልን ስለ አስተማራት «ከሣቴ ብርሃን ሰላማ» በማለት ሰይማዋለች

ይህች ታሪካዊት ቤተ ክርስቲ ያን በዘጠነኛውና በመካከለኛው የክርስትና ዘመን አንዳንድ ችግሮች ሳይገጥሙአት አልቀረም ። ይሁን እንጂ በመሥራችዋ በክርስቶስ እን ደተነገራት በጥበብና በየዋሃት ችግ ሮችን ሁሉ አሳልፋ እነሆ እስከ እኛ ዘመን ደርሳለች ።

ዛሬም ይህች በታሪክ፤በባህልና ሥርዐት በሥነ ጥበብና በሥነ ጽሑፍ የበለጸገችው ቤተ ክርስቲ ያናችን የዘመኑ ትውልድ በሚገባ እንዲያውቃትና ለተተኪውም ትው ልድ እንድትተላለፍ ሀልዎተ እግ ዚአብሔርን ማስተማር ስለ ድኅ ነተ ዓለም የምታበሥረውን ወን ጌል መስበክ የኃላፊነታችን ቀዳሚ መልእክት ነው ። ሀልዎተ እግዚ አብሔር ካልታወቀ ወንጌል ካልተ ሰበከ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው ከማንኛውም ድርጅት የምትለይ በት መንገድ አይኖርም ።

አዎ ለማንኛውም ሥራ ሠሪ አለው ፣ ሥራ ያለ ሠሪ ሊገኝ አለመ ቻሉን ዓለም ራሱ ያውቃል ። ለም ሳሌ ሥዕል ያለ ሠዓሊ መልክዐ ፊደል ያለ ጸሐፊ ሕንጻ ያለ ሐናጺ ሊገኝ አይችልም ፣ እንደዚህም ሁሉ ይህ ግዙፍ ዓለምና በውስጡ ያሉ ግዙፋን ፍጥረቶች እንዲሁም የማይ ታየው ረቂቁ ዓለምና በውስጡ ያሉ የማይታዩ ረቂቃን ፍጥረቶች ራሳ ቸው በራሳቸው አልተገኙም ሌላ ሠሪ አላቸው ። እርሱም እግዚ አብሔር ነው ። እግዚአብሔር ግን ለህላዌው አንዳች ምክንያት የለ ውም ። ይህንም ሁሉ በሃይማኖት እናረጋግጣለን ። (ዕብ ፲፩ ፣ ፫) ።

እንግዲህ የሕይወት ምንጭ የፍ ጥረታት ሁሉ አስገኝ የሆነውን አምላክ እንዴት በምን እናውቀዋ ለን የሚሉ ቢኖሩ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ወይም በሥራው ይታወ ቃል ። ዳዊት በመዝሙሩ ፲፱ ፣ ፩—፪ እንደዚህ ይላል «ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር ወግብረ እደ ዊሁ ያየድዓ ሰማያት» ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የእጁንም ሥራ ያወራሉ ። ቅዱስ ጳውሎስም ለሮሜ ሰዎች «ሀልዎተ እግዚአብሔርን ሲያስረዳ» ወዘኢያ ስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዐወቅበፍጥረቱለፍጥረቱ» ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር ለፍጥረ ቱ በፍጥረቱ ይታወቃል ብሎአል። (ሮሜ ፩ ፣ ፳) ። እንደገናም ይኸው ቅዱስ ጳውሎስ በግብረ ሐዋርያት ለልስጥራን ሰዎች («እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክርነት አልተወም ልባችንን ያስደስት ዘንድ በየጊዜው ዝናምን ይሰጣል ከረምትና በጋን ያፈራርቃል ዕፀዋትና አትክልት እን ዲያፈሩ ያደርጋል» በማለት የእግ ዚአብሔር መታወቂያው መገለጫ ው ሥነ ፍጥረቱና በየጊዜው የሚ ሠራው ሥራ መሆኑን አስተምሯ ል ። በዚህ አንጻር የምናያቸው ነገ ሮች ሁሉ የማናየውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እንዳለ ያስተምሩናል ።

የዘመኑም ፍጻሜ ሲደርስ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድ ንግል ማርያም ነፍስና ሥጋን ነሥቶ ሰው በሆነ ጊዜ ሥሉስ አካላት ዋሕ ደ መለኮት እግዚአብሔር በግልጥ ታወቀ ። ሰው የሆነው እግዚአብ ሔር ወልድ ስለሰው ልጆች ሁሉ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ በሦስተኛ ውም ቀን ተነሣከተነሣ በኋላ ባረገ በአሥረኛው በተነሣ በሃምሳኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ በመውረዱ ቅድ ስት ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች። መንፈስ ቅዱስ የወረደበትም ዕለት የቤተ ክርስቲያን የልደትቀን እየተ ባለ ሲታወስ ይኖራል ። ቤተ ክርስ ቲያን ዘለዓለማዊ በሆነው አምላክ ስለ ተመሠረተች ለዘለዓለም ጸንታ ትኖራለች ።

የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዓላማ ከላይ እንደ ተናገርነው ሀልዎተ እ ግዚአብሔርን ማስተማር ወንጌልን መስበክ ሲሆን ከዚህ ጋር ደግሞ ስለ ሰው ልጆች መብትና እኩ ልነት ነፃነትና ፍትሕ ስለ ዓለም ፀጥታና ሰላም የመናገርና መልእክ ት የማስተላለፍ ሰፊ ድርሻ አላት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰላም አምላክ የሰላም አሊቃ ስለሆነ «ሰላምየ አኀድግ ለክሙ ፣ ወሰላመ አቡየ እሁበክ ሙ» ሰላሜን እተውላችሁአለሁ ፣ የአባቴን ሰላም እሰጣችሁአለሁ በማ ለት ስለ ደገኛው ሰላም ተናግሮአል። በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያንም ሁል ጊዜ ስለ ሰ ላም ታስተምራለች ስለ ሰላም ትጸ ልያለች ። ነገር ግን ዓለም የወንዝና የድንበር የቀለምና የዘር ልዩነትን እየገነባ ስለ ሰላም ቢጮህ ስለ ትክ ክለኛ ፍትሕ ቢሰለፍ እውነተኛ



www.ethiopianorthodox.org

ሰላም ሊገኝ አልቻለም እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ዓለም የወንዝና የድንበር የቀለምና የዘር ልዩነትን ትቶ የመግረያ መፍጠር ዘመቻውንና ዛቻውን አቁሞ ሁሉም በእግዚአብሔር እኩል መሆኑን አምኖ ለሰላም ሲሰለፍ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች ።

ቤተ ክርስቲያን ከዓለሙ ጋር ያላት ሱታፌ በዚህ ብቻ አይወሰንም ቤተ ክርስቲያን በዓለም ያለች እንደ መሆንዋ መጠን ዓላማዋን ሳትስት በእቅዋሟ ጸንታ ማንኛውንም የኀብረተ ሰቡን ችግር ትካፈላለች ። ያልተማሩት እንዲማሩ የተቸገሩት ለጊዜው እንዲረዱ ለወደፊቱ ግን ራሳቸውን የሚረዱበትን ዘዴ እንዲያገኙ ወላጆች የሌሉአቸው ሕፃናት በሚገባ እንክብካቤ እንዲያድጉ ኅብረተሰቡ ጤናማ እንዲሆን ማንኛውም ዜጋ በኅብረተብነት የታነፀ እንዲሆን ሁሉም የተሻሻለ ኑሮ እንዲኖረው በሚያደረገው ጥረት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ዐቅምዋ በሚፈቅደው ሁሉ መርዳት እንዳለባት ታምናለች፣ ይህንም በተግባር ለመግለጥ ሰፊ ጥረት ታደርጋለች ።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፳፪ ዓ/ም ፩ኛ/ ለ፪ኛውና ለ፫ኛው ዙር መሠረተ ትምህርት ፕሮግራም ራስዋ የትምህርት መሠረትና ባለቤት እንደመሆንዋ መጠን ዓላማውን ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ባላት ኃይል ሁሉ እየረዳች ናት ። ወደፊትም መሃይምነት ከኢትዮጵያ እስከሚወገድበት ድረስ ለመሠረተ ትምህርት ያላትን ሰልፍ አታቋርጥም ።

፪ኛ/ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋ ችግር ወደ ደረሰባቸው ወገኖቻችን ከቅዱስ ሲኖዶስ ዓባላት መልእክተኞችን ልካ ሁኔታውን በመመልከት ካጠናች በኋላ የገንዘብ ርዳታ አድርጋለች ። ከእኅት አብያተ ክርስቲያናትም በድርቅ ለተጐዱ ወገኖቻችን የሚሆን እስቸኳይ ርዳታ ጠይቃለች ።

፫ኛ/ ቤተ ክርስቲያን የኀብረተ ሰቡን ችግር ማስወገድ የምትችለው በቅድሚያ በትምህርት የነቁና የበቁ ካህናት ሲኖሩ ነው ። ስለዚህም ባለፈው ዓመት ካህናትን ታሠለጥንባቸው የነበሩትን ፫ ማሠልጠኛዎች ወደ ፭ ከፍ አድርጋለች።

፬ኛ/ ለምእመናን መብዛት ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ለወንጌል መስፋፋት ዋናው ምክንያት የመንፈሳውያን አባቶች በብዛት መኖር መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ በማመኑበት ባለፈው ዓመት ከተሾሙት ፲፫ ጳጳሳት ሌላ በዚህ ዓመት ፫ ጳጳሳት በምእመናን እስመርጣ ሾማለች ።

፭ኛ/ ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊት እንደ መሆንዋ መጠን ምእመናን ለልማት በሚሠሩበት ሁሉ እየተገኘች ማስተማርና ምእመናን ማበረታታት ዋና ዓላማዋ መሆኑን ታምንበታለች ስለዚህም በተፈጥሮ ድርቅ ምክንያት ቀደም ሲል ይኖሩበት ከነበረው ቦታ እየተዛወሩ ለልማት እመች በሆነ ቦታ ለሰፈሩ ኢትዮጵያውያን እንደአስፈላጊነቱ ቤተ ክርስቲያን ለመትከልና የኀብረተ ሰቡን ችግር ተካፋይ ለመሆን እየተዘጋጀች ናት ሠርቶ መኖር በእግዚአብሔር ቃል የታዘዘ እንደመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም «ድሆች እንዳትሆኑ ስንፍናን አትውደዱ» (ምሳሌ ፳ ፣ ፲፫) የስንፍና ብዛት ጣርቅ ለባሽ ያደርጋል (ምሳሌ ፳፫ ፳፩)።

መሬትህን ለራስህ በእርሻ አዘጋጀት (ምሳሌ ፳፬ ፳፯) እናንተ በሬና አህያ እየነዳችሁ በውኃ አጠገብ ሁሉ ዘር የምትዘሩ ብፁዓን ናችሁ(ኢሳ ፴፪ ፳) የማይሠራ አይብላ (፪ተስ ፫ ፣ ፯—፲፫) እያለች የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ሁሉም ሠርቶ ኑሮውን ማሻሻል እንዳለበት ስለ ልማት ታስተምራለች በተግባርም ታሳያለች ። እግዚአብሔር ሰውን ከፈጠረው በኋላ የተፈጠረባትን ምድር ተክል እንዲተከልባት ዘር እንዲዘራባት ጕርፍና ማዕበል እንዳይበላት ግድብ በመገደብ ዛፍ በመትከል እንዲንከባከባት ትእዛዝ ሰጥቶታል ።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በታነጸችበት ቦታ ሁሉ ደን አልምታ አካባቢዋን በሚገባ ተንከባክባ ይዛ ትገኛለች ። ለምሳሌ ይህን ለማወቅ ቢያስፈልግ የኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደ ቦታው ሁኔታ ዕድናዝግባ ወይራና ግራር ቀርቃሐና ሾንበቆ ወዘተ -- አልምታ በዚህ ዐሉ አሸብርቃ ትታያለች ።

እንግዲህ ልማት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንግዳ አይደለም ኢትዮጵያውያን ካህናት ዛሬውንም ቢሆን እርሰው ቆፍረው ቀለም በጥብጠው ብራና ፍቀው ዳምጠው ጽፈው ደጕሰው ቤት ሰቦቻቸውን ከማስተዳደር ጋር ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉና ምእመናንን ሲያስተምሩ መኖራቸው ቤተ ክርስቲያኒቱ በልማት በኩል ያላትን እንቅስቃሴ ያስረዳል ።

ነገር ግን ትምህርቱም ሆነ ልማቱ ጊዜው በሚፈቅደው ሁኔታ በዘመናዊ አቅድ በዘመናዊ መገሪያ ቢሆን ከልማዳዊው የሥራ ይዘት ይልቅ የበለጠ ውጤት እንደሚያስገኝስለሚታመን ቤተ ክርስቲያን ዓላማዋን ሳትዘነጋ በእቅዋሟ ጸንታ ጊዜውንና የዘመኑን ትውልድ ተከትላ መራመድ ይኖርባታል ።

ጊዜው የሥራ ነው ጊዜው የትምህርት ነ ው የምእመናን ጆሮወደ ትምህርት አዘንብሉአል እእምሮአቸው ምሥጢራትን ለመቀበል ተዘጋጅቶአል ትውልዱ ጥያቄ ያቀርባል እጥጋቢ መልስም ይፈልጋል ምእመናንም ከምን ጊዜውም ይልቅ ወደ ቤተ ክርስቲያን በብዛት ሲመጡ ይታያሉ ። ስለዚህ ራሳቸውን ለወንጌል አገልግሎት መሥዋዕት ያደረጉ ወንጌላውያን ያስፈልጋሉ እግዚአብሔር እውነተኞች መምህራንን ያበዛ ዘንድ ቤተ ክርስቲያን እጆችዋን ለጸሎት ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ከምድረ ኢትዮጵያ ረኃብን ማይምነትን በሽታን የምራል ውድቀትንና እስጸያፊ የኑሮን ሥርዐት ለማስወገድ የሚያደርገው የኀብረት ዘመቻ የተሳካ እንዲሆን የቤተ ክርስቲያናችን የዘወትር ጸሎት ነው ።

የሰላም አምላክ እግዚአብሔር
ለዓለም ሁሉ ሰላምን ትክክለኛ ፍትሕን
ነፃነትንና እኩልነትን ይስጥልን።
እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ይባርክ ።



# ለ፬ኛው ዓመት በዓለ ሢመተ ፓትርያርክ የቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ ያደረጉት ንግግር ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ

በቤተ ክህነት ሠራተኞች ስም መልካም ምኞቴን እገልጣለሁ ።

ዝቅተኛውም ማዕረግ ያለእግዚአብሔር ፈቃድ እንደማይሰጥ ታላቁ



አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አሥኪጅ ንግግር ሲያደርጉ ።

እንኳን ለ፬ኛው ዓመት በዐለ ሢመትዎ በሰላም አደረሰዎ እያልሁ

እንኳን የመጨረሻውን የቤተ ክርስቲያን ርእስነት መቀበል ቀርቶ

መጽሐፍ ያስተምረናል ። በእግዚአብሔር ፈቃድ የቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

አገልጋዮችና ምእመናን ተሳታፊዎች የሆኑበት የፓትርያርክ ምርጫ በሚካሄድበት ጊዜ ገጥሞን የነበረው ከፍተኛ ችግር ዕጩ የሚሆኑት ተወዳዳሪዎች ከብፁዓን ጳጳሳት ብቻ ይሁን? ወይስ አበው መነኮሳት ይሳተፉበት የሚለው ርእስ ነበር ። «ጳጳሳት» ብቻ የሚለው የጥቂት ሰዎች ሐሳብ ተፈጽሞ ቢሆን የአሁኑ ሁኔታመልኩን ይለውጥ ነበር።የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆነና ከእግዚአብሔር በስተቀር ማንም ያላሰበው ተግባር ሊፈጸም ቅዱስነትዎ በብሕትውና ዓለም በነበሩበት ወቅት ባሕታዊ ብቻሳይሆኑ በተግባር የተተረጎመ ውጤት በማሳየትዎ እብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ት/ቤቶችን በመሥራት መዋዕለ ሕፃናትን በማዘጋጀት ፣ በትሩፋትና በገድል የተወሰኑ በመሆንዎ ለዚህ የመጨረሻ ማዕረግ በቅተዋል ። ፍቅረ ንዋይና ፍቅረ መባልዕት ወመስቴ ከአጠገብዎ ስለራቀ ሌላው ገድል ነው ማለት ይቻላል ።

ከዚህ ቀጥዬ የምገልጠው ባለፈው አንድ ዓመት ከአሥር ወር ምን ተፈጸመ? ምንስ ታቀደ? የታየው የሥራ ውጤትና ድክመት ምንድን ነው ? ብዬ ነው የማቀርበው ። ይህን ፣ የምዘረዝረው የሆነውን ብቻ ለመናገር ነው ። ከመንቀሳቀሳችን የተነሣ የተፈጸመ ስሕተት እንኳ ቢኖር እናርማለን ፣ እንታረማለን ፣ ሌላ ጉዳይ የለም በዚህ አድማችን የማይደሰቱ ቢኖሩ እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው እንላለን ።

፩/ በሕመምና በእርግና የደከሙ አበውዕረፍት እንዲያደርጉ በተወሰነው መሠረት በእግራቸው የሚተኩ ፲፯ ብፁዐን ጳጳሳት ተሾመዋል ። ከነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ በሀገር ትምህርት ብቻ ሳይሆን በውጭ ሀገርም በቂ ሙያ ያላቸው ስለሆኑ አንዳንዶች ፍሬ እያሳዩ ናቸው ። ምሁራን አበው ከምሁራን ካህናት ጋር ተባብረው መሥራት እንደሚገባቸው ሳንጠቁም አናልፍም ።

፪/ ከአብዮታዊ መንግሥት በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ወደ ፳፻ የሆኑ የቤተ ክህነት ሠራተኞች የድጎማ ደመወዛቸውን እንደያዙ ወደመንግሥት መ/ቤት በመሄድ ቋሚ ሠራተኞች ሆነዋል አብዛኛዎቹም ፍሬ እያሳዩ ራሳቸውን ጠቅመው ሀገርንም እያገለገሉ ነው ። ይህ በመሆኑ አንዳንድ የወሬና የፀሐይ መሞቅ ጓደኞቻቸው እንደሚሉት ሳይሆን ሠራተኛውየሄደው «የቦዘኔ ደመወዝተኛ ነን» ብሎ ባሳለፈው ሐሳብና ጥያቄ ሳቢያ የተፈጸመ ነው ።

፫/ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት ካህናትን ለማሠልጠን የሰበካ ጉባኤን በይበልጥ ለማደራጀት ወጣቶችን የኅብረተሰብ ልማት ተሳታፊ ለማድረግ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሳብ ፣ የገዳማትን ህልውና በተቻለ መጠን ለመንከባከብ ከ፫ሚሊዮን ብር ያላነሰ ለ፫ ዓመት ተፈቅዶልናል ። የካህናት ማሠልጠኛው በአምስት ሀገረ ስብከት ሥራ በመጀመር ላይ ነው ። የሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ ተሳትፎ እየታየበት ነው ።

፬/ በቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ የመጀመሪያ የሆነው የቅዱስነትዎየኢየሩሳሌም ይፋ ጉብኝት ለጥንት ይዞታችንም ሆነ ለሌላው ታላቅ ውጤት በመሆኑ ጉዞውን ካዘጋጁት ዓባላት ጋር የኢየሩሳሌም መታሰቢያድርጅትም አብሮ ሲታወስ የሚኖር ነው ። ከታሪካችን መዝገብ ጋር ተቀርጾ ይኖራል ።

፭/ ሀገራችን በተፈጥሮ አደጋና ፤ጦርነት በተመታችበት ወቅት ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ምንደኛ ወይም አብዮት እንደመጣባቸው ከፍሎች ዝም ብላ አላየችም ። ለመልሶ ማቋቋምና ለመሠረተ ትምህርት ዘመቻ ከሩብ ሚሊዮን ብር ያላነሰ ለግሳለች በዚህም ጉዳይ ከሚመለከታቸው መንግሥታውያን አካላት የምስክር ወረቀት አላት ።

፮/ አንዳንድ የሃይማኖት ድርጅቶች አብዮትን እንደመጣባቸው መዓት አድርገው ሲያወግዙ፣ስም ሲያጠፉ ፣ ውሉ የጠፋና የደፈረሰ ወሬ ሲያወሩ ቤተ ክርስቲያናችን በይፋ ወጥታ የሐሰቱን ዜና አስተባብላለች ። እንደመላው ኢትዮጵያዊ ገባርና ጪሰኛ የነበሩ ካህናት ዛሬ የመሬትናየከተማ ቦታ ባለቤት በመሆናቸው የገበሬና የቀበሌ ማኅበር ሊቃነ መንበር እየሆኑ በማገልገል ላይ ናቸው። ስለዚህቤተ ክርስቲያን ለአብዮቱ የማያወላውል ድጋፍ አላት።

፯/ ቤተ ክርስቲያኒቱ ንዋየ ቅድሳት ታደራጅበት የነበረ የእንጨት መሰንጠቂያ ድርጅት በአንዳንድ የቤተ ክህነት ሠራተኞች ደባ ተወስዶ ሳለ ከአብዮታውያን ድርጅቶች ጋር ባደረግነው ድርድር ተመልሶ በቁጥጥራችን ሥር ይገኛል። በምርትም ላይ ነው።

፰/ ለብዙ ጊዜ ሥራው ተቋርጦ የነበረው የሻማ ማምረቻ እንደገና ተንቀሳቅሶአል ። ስለምርት ካነሣን ዘንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ አንጡራ ገንዘብ የሆነው የኅሩ ገብርኤል ተግባረ እድ ማሠልጠኛ እንዲሁም ሌሎች የማምረቻ ድርጅቶቻችን የሥራ እንቅስቃሴ ደስ የሚያሰኝ ነው ። በዚህም ተግባር ጉዳዩ የሚመለከታቸው አብዛኛዎቹ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች የሚያሳዩት መሯሯጥ ደስ ያሰኛል ።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ራሷን እንድትችል ሁል ጊዜ የሚነገረው ሁሉ ተግባራዊ ካልሆነ የገበያ ዘመድነት ይሆናል። መስቀል ጽንሃ ፣ ጸናጽል መቋሚያ ፣ መንበር ፣ ማሕፈድ ፣ ዐውድ ፣ ልብሰ ተክህኖ የመሳሰሉት ሁሉ በቁጥጥራችን ስር ሆነው እኛው አምርተን እንድንጠቀምባቸው ያስፈልጋል ። የግለሰቦች መበልጸጊያ ሆነው የምንበዘበዝባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት የግል ሀብታችን የሚሆኑበትን ጊዜ በተስፋ እንጠብቃለን ።

እስከዚያውም ድረስ ቤተ ክርስቲያኒቱ እጅዋን አጥፋ አልተቀመጠችም። እንደ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ያሉት ለበጎው ልማት ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው ። አንዳንዶቹ ደግሞ ባመት ካላቸው የሰበካ ጉባኤ አባላት ቁጥር አንድ እንኳ ሳይጨምሩ ስዕለትና ሙዳየ ምጽዋት ብቻ እየቆጠሩ ሲበሉ ስናይ እናዝናለን ።



፱/ የአዲስ አበባ አድባራት ክልላቸው በተለይ ያንዳንዱ ደብር ይዞታ በከተማ ልማት ቤት ሚኒስቴር በኩል እየተጠና በካርታ ንድፍ መስጠት ስለጀመረ አልፎአልፎ ከአንዳንድ ቀበሌዎች ጋር የነበረ ንን አለመግባባት ይፈታዋል ብለን እናስባለን ። በዚህም በኩ ፣ ትብብር ሚኒስቴሩን ስናመሰግን በውኸር ንብር ጊዜ የተወሰዱ የፓትርያርኩ መገልገያ ቤቶች በቅርቡ እንደሚመለሱ ቃል ተገብቶልናል ።

፲/ ለግለሰብ ነጋዴ መበልጸጊያ የነበረው የቁልቢ ገብርኤል ንዋየ ቅድሳት ወደ አዲስ አበባ መጥቶ ለምእመናን በተመጣጠነ ዋጋ እንዲሸጥ በመደረጉ ያስብነውን ያህል ባይሳካልንም ባመት ውስጥ ከ፩፻ ፳ሺ ብር በላይ ተሸጦ አሁን ያለው የዚህ እጥፍ ነው ። አልፎ አልፎ የሚሸረበውን ሴራ ስንበጣጥስከዚህ የበለጠ እንደምንሠራ ይታመናል ።

፲፩/ ውል ቅጡ የጠፋው አንዳንድ ግለሰቦችም በገንዘብ ጉድለት እየተጋለጡበት ያለ የትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ጉዳይ ወደፊት በሰፊው ይገለጣል ።

፲፪/ የጥቂት ግለሰቦች መበልጸጊያ የሆነው የብራና ድርጅታችን በቅርቡ መፍትሔ ይገኝለታልብለን ተስፋ እናደርጋለን ። ጉዳዩ የሚመለከታቸውም እንደገና እያጠኑት ነው አብዮታዊው መንግሥት የቤተክርስቲያኒቱን መመሪያ አጽድቆ እስኪሰጥ ድረስ ባለን ኃይል መንቀሳቀስ በማስፈለጉ አሁን የተያዘው የቅዱሳት መጻሕፍት ማሳተም ጉዳይ ተስፋ የሚጣልበት ሆኖአል ። የመንፈሳዊ ኮሌጅ ጉዳይም ለመንግሥት ቀርቦ እየተጠና መሆኑን የከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ገልጦልናል በቅርቡ ተሰብስቦ የነበረው ቅዱስ ሲኖዶስ ስለባሕታውያን ስለወጣቶችና ስለሰንበት ማኅበራት የሰጠው ውሳኔ በሥራ እስኪተረጎም ድረስ አንዳንድ ክፍሎች ለግል ጥቅማቸው የሚያደርጉት መሯሯጥ ቢኖርም መልክ እየያዘ ነው። የአንዳንድ ወጣቶች ማልቀስ ገላወን ሲያጥቡት እንደሚያለቅስ ሕፃን አይነት ስለሆነ ጥቅሙን ሲያውቁት ይተውታል እንላለን ።

፲፫/ እጅግ እንገብጋቢ ሆኖ የሚገኘው ቤተ ክህነትን ዕድሜ ልክ አገልግለው የዘለቂታ ጡረታ የሌላቸው ካህናትና ጥቂር ራሶች ጉዳይ ነው ። ይህ የመብት ጥያቄ የብሔራዊ አገልግሎት ጥያቄ እንጅ ትሩፋት አለመሆኑ ተገልጦ ለአብዮታዊው መንግሥት የቀረበው መጠይቅ የተስፋ መልስ ይገኝበታል ብለን እየተጠባበቅን ነው ።

የቤተ ክህነት ሰው የዘለቂታ ጡረታ አያስፈልገውም የሚሉ ክፍሎች ካሉ ይቅርታ የሌለው ኢሰብአዊ ተግባር ስለሆነ ሊታረም ይገባል ። መንግሥት በሀገር ውስጥ ያሉትን ሕዝቦችበትክክል ማየት ዋና ተግባሩ ስለሆነ ብሔራዊ አገልግሎት እየሰጡያሉትን ሰዎች መብት የሚያሳጣ አድራጎት እስካልፈጸሙ ድረስ በትክክል ይንከባከባቸዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

ቤተ ክህነት የመክሰስና የመከሰስ ባሕርይ ስለነበረባት ድርጅትም ስለሆነች ከግለሰቦችም ሆነ ከሌላ ድርጅት ጋር በምታደርገው ክርክር አንዳንድ ነገረ ፈጆች ከባለ ጉዳዮች ጋር እየተመሳጠሩ የፈጸሙት አሻጥር ብዙ ነው ። የእነሱንም ፍርድ ለታሪክ ሰጥተን መተው ብቻ ሳይሆን እኛም እንፋረዳቸዋለን በቤቱ የሚመጣው ዕዳ በነሱ ሰበብ ስለሆነ የሕሊና ዕረፍት ያገኙሉ ብለን አናስብም ።

ምሥጢሩ ርቀት እንኳ ሳይኖረው ፩፻፶ ዳቦ ከመላስ አንዱን መጎርደም ዋጋ አለው የሚባል ዘይቤ አለ ። ብዙ ካህናት መነኮሳት ዲያቆናት አሉን ብለን ከምንናገር ጥቂቶችን በራስ አገዝ ተግባረ እድ ሥራ አሠልጥነን ወደ ሕዝብ በመላክ ሠርተው እንዲያሳዩ ማድረግ አለብን ። የካህናት እጅ ዝንት ዓለም መቀበያ መሆን ስለማይገባው አንድቀን ሠርቶ መስጠት እንዲማር በዚህ ተግባር መገፋፋት ይገባናል ። ከጧት እስከማታ የተንዘረፈፈ ልብስ ለብሶ ማታ ጠም ከማደር ልብሱ ለበዐል ቀን ሆኖ ባጭር ታጥቆ መሥራትን መልመድ ይገባል «እየሠሩ ማስተማር እያስተማሩ መሥራት» የካህናት መርሕ መሆን አለበት እንላለን በዚህም ብተግባረ እድ የተመሰከረው የቅዱስነትዎ አመራር ይደግፈናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን ።

እንደጎረቤቶቻችን እስከንሆን እንደ ቤታችን እንሠራለን ። የምንጠይቀው ሐቅና እውነት በግቢአችን እንዲሰፍር ነው።ግቢአችን የሰላምና የፍቅር ድሃ ነች ። አንዳንዱ ሠራተኛ የገንዘብ ሳይሆን የሐቅ ድሃ ነው ። በቂ ሥራ ካለመኖሩ የተነሣ አድማ ፣ ወሬ ሰብቅ አልፎ አልፎ ይታያል ። ታዲያ በዶዎጋን መብራት ሲመለከቱት አይጥ የተነፈሰበት ማግ ሆኖ ይቀራል ። ዛሬ አዲስ ወሬ ይፈለሰፋል ከሰዓት በኋላ ይከሰማል ። በማግስቱ ሌላው ይፈጠራል ከሰዓት በኋላ የባሰው ይመጣል ። በስምንት ቀን ውስጥ ሁሉም ይከሽፋል ታዛቢ ግን ምን ዓይነት ቤት ነው ይላል ። እንዳንዶቻችን ሁሉን የመሸከም ዕድል ተሰጥቶን ለሚወራው ሁሉ አንበረገግም ። በሰብአዊ ተፈጥሮ መነጽር ሲታይ ግን ከንጹሕ ሕሊና የተራቆተ አካልነው፣ የሚያነሣንም ሆነ የሚጥለን የሐሳውያን ወሬ ሳይሆን ሥራችን ነው። በሥራው የሚተማመን በወሬ አይደነብርም ። በዚህ በኩል ፈጣሬ ሰማይ ወምድር ከአጠገባችን አለ ።

በጠቅላላው የቤተ ክህነትን ተግባር በተሊያየ መጠን ፈር ለማስያዝ የቅዱስነትዎ ጸሎት የብፁዐን አባቶች ኅብረት የእውነተኞች የቤተ ክህነት ሠራተኞች ርዳታ እንዳይለየን እንጠይቃለን ። ለወሬና ለሰብቅ የማንሸበረውን ያህል ባለን አቅም ለመሥራት ወደኋላ አንልም። ሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲጠብቅ እየጸለይን ዘመናችን የሰላምና የምርት እንዲሆን እንመኛለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ፓትርያርኩ ለዘመን መለወጫ ያስተላለፉት ቃለ በረከት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የ፲፱፻፹፫ ዓ/ም የዘመን መለወጫውን በዓል ምክንያት በማድረግ ጳጉሜን ፭ ቀን ማታ በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚከተለውን ቃለ በረከት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን አስተላልፈዋል ።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ።
በከተማና በገጠር የምትገኙየተወደዳችሁ ምእመናን የሕይወት ጌታ እግዚአብሔር ለዚህ አዲስ ዓመት ሁላችሁንም እንኳን በደኅና አደረሳችሁ ።

መዝሙር ፩፻፲፫ ቊጥር ፳፮እኛ ሕያዋንእግዚአብሔርን እናመሰግና ለንዘተብሎ እንደትነገረውሁሉ እሁንምእኛ ሕያዋን በሕይወት እንኖር በት ዘንድ ስለተሰጠን ስለዚህጊዜና ዘመን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን ።

ዓመተ ዓለም በዓውደ ፀሐይ እንደሚሰፈርና እንደሚቆጠር የሰው ልጅ፡ኑሮም እንዲሁ በዓውደ ዓመት ይሰፈራል፣ ይቆጠራል ። ይህ ስለሆነ እቻንዳንዱ ዓውደ ዓመት በአዲስነት ስለሚታይና በዚህም አዲስ ዓመት የሰው ልጅ በአዲስ መንፈስ ለአዲስ ሥራ ስለሚሰለፍ በየዓመቱ የሚደረገው የዘመን ለውጥ የሕይወትንም ለውጥና ተሐድሶ ያስተምረናል ።
እግዚአብሔር ሰውንና ጊዜን የፈጠረው ለሥራ ስለሆነ እንሠራበት ዘንድ የተሰጠን ጊዜ በከንቱ እንዳያልፍ ምን ጊዜም የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ፈቃድና ፍላጎት ነው ። በዚህ የሞትና የሕይወት ዓለም ላይ የሰውን ቅድስና በሚያረጋግጥ ሕይወት ለመኖር ምን ጊዜም ትጋሄ ያስፈልጋል። ይህ ከሆነ ዘንድ ዕለታትና ዓመታት በተለዋወጡ ቁጥር ለአዲስ ሕይወት በአዲስ መንፈስ መሰለፍ በእርእያእግዚአብሔር ከተፈጠረ የሰው ልጅ ሁሉ የሚጠበቅ የኑሮ ግዴታ ነው።ይህም አዲስ ሕይወት ዛሬም ሆነ ወደፊት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ በአዘጋጀው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መኖር የሚያበቃ ሊሆን ይገባል ።

ቅዱስ መጽሐፍ የሰው ልጅየሚኖርበትን ዓለም በተክል ቦታ በመመሰል ፍሬ የማያፈራ ተክል በእትክልት ቦታ መኖር እንደማይችል ሁሉ የሰው ልጅም እንዲሁ ያለ መልካም ሥራ በዚህ የሥራ ዓለም ላይ መኖር እንደማይገባው ያስጠነቅቃል ።ሉቃ ፲፫ ፤ ፮ ።

ይህ ቃል በአጭሩየሰው ልጅ ህልውና የሚወሰነው በሥራ መሆኑንና በዚህ ዓለም ላይ በክብር ለመኖርም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሥራን ጊዜ በሥራ ማሳለፍ እንደ ሚያስፈልግ ያስረዳል ። ስለዚህ አዲስ ዓመት አሁንም በአዲስነት የምንቀበለው ሞተ ሕሊናን በትንሣኤ ልቡና በማስወገድ በሰውና በእግዚአብሔር ፊት ደስ የሚያሰኝ መልካም ሥራን ለመሥራት በመዘጋጀት ሊሆን ይገባል ።

ወርኃ መስከረም ክረምትና በጋ የሚፈራረቁበት ፤ አዲስ ሰማይ አዲስ ምድር የሚታይበት፤ ተናፋቂ ወቅት በመሆኑ በዚህ ወቅት የኢትዮጵያ ዓውደ ዓመት መከበር አዲሱን ዓመት በእርግጥ አዲስ ያደርገዋል ። በዚህ የመሸጋገሪያ ወቅት የኢትዮጵያ ሜዳዎች ተራሮችና ሸንተረሮች ልምላሜን ተጎናጽፈው ተመልካችን ያስደስታሉ ። አዝርእትና አትክልትም የሠራተኛችን የድካም ዋጋ በእጥፍ ለመክፈል የበረከት ፍሬን በእጥፍ ተሸክመው ይታያሉ ። ይህም በአጠቃላይ የምንኖርባት ምድር የተፈጥሮ ጸጋና የነዋሪዎችንም የተፈጥሮ በረከት አጉልቶ የሚያሳይ ከመሆኑም በላይ እንኖርባት ዘንድ ከተሰጠችን ከዚህች ቅድስት ምድር ጋርም በይበልጥ የሚያስተዋውቅ በመሆኑ ይህን በተወሰነ ጊዜ ታይቶ የሚረግፈውን ልምላሜና ፍሬ ምን ጊዜም የሚቀጥል ዘለዓለማዊ ለማድረግ በዕርግጥ አዲስ መንፈስና አዲስ ሥራ ያስፈልጋል ። ይህም ምኞትና ፍላጎት ተግባራዊ የሚሆነው የተፈጥሮ ድህነት በሌለባት በዚች ቅድስት ምድር ላይ ያለ ድህነት ወይም ያለረኃብና ችግር መኖር ሲቻል ነው ።

በምድር ላይ የተሟላ ሕይወትን መኖር የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከመጥራት ስለሚያድን የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ በሚኖሩበት ዓለም ላይ ሁል ጊዜ የሥራ ወይም የተግባረ እድ ሰዎች መሆን ይገባቸዋል ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የተማረ እንዲያስተምር ያልተማረ እንዲማር የተራቆቱ ምድረ በዳዎች አረንጓዴ ልምላሜ እንዲለብሱ በድርቅ ምክንያት የሚራቡትና የሚጠሙት ወገኖቻችን ከምድር ፍሬ እንዲጠግቡ ፤ በሽታ እንዲጠፋ የምታደርገውን ከፍተኛ ጥረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከልብ ትደግፋለች ፤ በአለፈው እንደአደረገችው ሁሉ ወደፊትም የዚህ መልካም ተልእኮ ተባባሪነቷን በተግባር ትገልጣለች ።

የዓለም ሠራኢና መጋቢ የሆነው አምላክ ዝናምን ለዘር እንዲሰጠን ጠልንም ለመከር በመስጠት ዘመኑ መከርን ይባርክልን ።

ለዓለም ሰላምን ይስጥልን ።
አዲሱን ዓመት የሰላም የሥራና የብልጽግና ዓመት ያድርግልን።
ሀገራችንን ኢትዮጵያን በአንድነትና በነፃነት ለዘለዓለም ይባርክ።



# ዓ ለ ም አ ቀ ፍ ዜ ና ዎ ች

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላይ ምክር ቤት የማእከላዊ ኮሚቴ ከነሐሴ ፰ ቀን እስከ ፲፮ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ድረስ በጀኔቫ ጠቅላላ ስብሰባ አድርጎ በመንፈሳዊና በማኅበራዊ ጻጉይ ፤ እንዲሁም በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ በሰፊው ከተወያየበኋላ ውሳኔዎችን ያሳለፈ መኾኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በመወከል በስብሰባው ላይ ተሳትፈው የተመለሱት አቶ መርስዔ ኅዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ተ/ዋና ሥራ አስኪያጅና የኮሚቴው አባል ገለጹ ።

ጉባኤው ከተነጋገረባቸው አርእስተ ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ሀብታም ሀገሮች በልማት ወደኋላ ለቀሩ አገሮች ርዳታ መስጠት እንዳለባቸውና እያንዳንዱ አባል ቤተ ክርስቲያንም ካላት ገቢ እየቀነሰች ድኾች ራሳቸውን የሚችሉበትን ድርጅት ማቋቋም እንዳለባት በተለይም የምስተኛው ዓለም ሕዝብ ምግብ ፤ መጠለያ፣ ልብስ በማጣት እየተሠቃዩ ኀያላን መንግሥታት የሰውን ልጅ በቅጽበት ከገጸምድር የሚያጠፋ የጦር መሣሪያ ለመግዛት በሚሊዮን የሚቈጠር ብር ማውጣት እንደሌለባቸውና ዓለምን ከከባድ ሥጋት ላይ የጣለው የኒኩሌር ጦር መሣሪያ እሽቅድድም እንዲቀነስ አሳስቧል ፤ እንዲሁም አንዳንድ ኀያላን መንግሥታት በተለይም አሜሪካ በኢሮፕና በእስያ የምታደርገውን ወታደራዊ ክምችት እንድትቀንስ በሚለው ሐሳብ ላይ ተወያይቷል ።

በተለይም ሴቶች በቤተ ክርስቲያንና በኅብረተሰብ ዘንድ ሙሉ ተካፋይ እንዲኾኑ ሐሣብ ቀርቦ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል እንዲሁም አንዳንድ ሀገሮች ለነጻ ነታቸው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በማፈን እንደደቡብ አፍሪካ ፣ እኤልሳ ልባዶርና እንደ ደደቡብ ኮሪያን የመሳሰሉት ሀገሮች በሚያደርጉት ተጽዕኖ ላይ ጉባኤው የወግዘት ቃል ያስተላለፈ መኾኑን አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ አስረድተዋል ።

በተጨማሪም በደቡብ አፍሪካ የሚካሄደውን የነጻነት ንቅናቄ ጉባኤው በሙሉ ልቡ ደግፎ ለጊዜው አንድ ሚሊዮን ዐምስት መቶ አምሳ አ ን ድ ሺሕ ብር ረድቷል ፣ ከዚህም ጋር የዘር መድልዎን እየተከታተለ ለጉባኤው መግለጫ የሚያቀርብ ክፍል ከተቋቋመ ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ቢኾንም ሥራውን በቀለጠፈ ሁኔታ ለማካሄድ የሰው ኃይል እንዲጨመርለት ጉባኤው የወሰነ መኾኑን አቶ መርስዔ አስረድተዋል ።

ጉባኤው ሥራውን ባካሄደበት ወቅት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊ የኾኑትን ዶክተር ፊልፕፖተርን በዋና ጸሐፊነቱ ሥራ እንዲያገለግሉ በድጋሚ ለ፭ዐመት ሾሟቸዋል ፤ ፫ ረዳት ዋና ጸሐፊዎች ምየተሾሙ ሲኾን ከነዚህም ረዳት ጸሐፊዎች ውስጥ ከአፍሪካ የግብጽ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባል የኾኑት ወ/ሮ (ሚስስ )ኤም አሳድ እንደሚገኙበት አቶ መርስዔ ገልጸዋል ።

ከዚህም በስተቀር ጉባኤው በርከት ላሉ የምክር ቤቱ ባለሥልጣኖች የኮንትራት ሹመት ሰጥቷል ኮንትራታቸው ከተራዘመላቸው ሹሞችም መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዓባል የኾኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን እንደሚገኙበት አቶ መርስዔ አስ ታውቀው በመላው ዓለም የሚገኙት የክርስቲያን ቤተሰቦች በተገኙበት በዚሁ ጉባኤ ላይ ፫፻፴፪ አባላት የተሳተፉ ሲኾን ።

፭ኛ/ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ የጎጃም ክፍል ሀገር ሊቀ ጳጳስ የቡድኑ መሪ በመኾን እንዲሁም ራሳቸው አቶ መርስዔ ኀዘን አበበ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመወከል የተገኙ መኾናቸው ታውቋል ።



www.ethiopianorthodox.org



የዓለም አብያተ ክርስቲያናት የማዕከላዊ ኮሚቴ ሰብሳቢ በተካሄደበት ወቅት

# በናይሮቢ የተዘጋጀው የኅትመት ሥራ ባለሙያዎች ሴሚናር ተፈጸመ ።

እንደ አውሮፓ ዘመን አቈጣጠር ከነሐሴ ፪—፲፮/ ፲፱፻፹ ዓ/ም የዓለም ክርስቲያናች የመገናኛ ዘዴዎች ማኅበር ፣ «ወርልድ አሶሲየሽን ፎር ክርስቲያን ኮሚኔኬሽን» በናይሮቢ ከተማ በአዘጋጀው የሕትመት ሥራ ባለሙያዎች ሴሚናር ላይ ጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በተለይም በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም ተቋቁሞ ለብዙ ዓመታት ቅዱሳት መጻሕፍትን በማዘጋጀትና በማተም ላይ የሚገኘውን «የትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ ቤትን በመወከል የማ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገ/እግዚአብሔል ሴሚናሩን ተሳትፈው ተመልሰዋል ።

በሴሚናሩ ላይ ተካፋይ የነበሩት ፣

| | | |
|---|---|---|
| ፩/ | ከኢትዮጵያ | ፪ |
| ፪/ | ከኬንያ | ፰ |
| ፫/ | ከሱዳን | ፩ |
| ፬/ | ከማላጋሲ | ፩ |
| ፭/ | ከጋና | ፪ |
| ፮/ | ከግብጽ | ፩ |
| ፯/ | ከዝምባብዌ | ፩ |
| ፰/ | ከኢንግላንድ | ፪ |
| ፱/ | ከምዕራብ ጀርመን | ፩ |
| ፲/ | ከዩጋንዳ | ፪ |
| ፲፩/ | ከዛምቢያ | ፩ |
| ፲፪/ | ከማላዊ | ፩ |
| ፲፫/ | ከናይጀሪያ | ፪ |

ጠቅላላው ከ፳፭ በላይ የሚሆኑ የሕትመት ሥራ ባለሙያዎች በሴሚናሩ ተሳታፊዎች ሲሆኑ ስለ ሕትመት ሥራዎች ልዩ ሙያ ያላቸው ምሁራን ተመድበው በቂ ትምህርት የሰጡ መሆናቸውን ሊቀ ካህናት ብርሃኑ ገልጸዋል ።

ከዚህም ጋር ተወካዮቹ ስለ ሥራቸው ማለትም ስለ አሳተሚቻቸውና ወደፊትም ስለ ሚያሳትሙአቸው መጻሕፍት በፕሮግራም ተመድቦ ገለጻ ተደርጎአል ፣ በየአንዳንዱም ገለጻ ላይ ትችት ፣ ጥያቄና መልስ ተደርጎበታል ።

ክርስቲያናዊ ሕይወትና ስሜት ያለው ሁሉ ከታሪክ ማኅደር እንደሚረዳው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊት እንደመሆኗ መጠንምዕመናንን በሃይማኖት የሚያጸኑ ፣ በሥነ ምግባርየሚያንጹ ፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት የሚመሩ እጅግ በጣም ጥንታውያን የሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍት ፀጥንዶግቱ ፣ በየአድባራቱና በየገጸር አብያተ ክርስቲያናቱ በብዛት ያሏት መሆኑን ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ከላይ የተጠቀሱትን ጥንታውያን ቅዱሳት መጻሕፍት ለትውልድ ሊያቈዩና ሊያስተላልፉ የቻሉት እንደ ዛሬው የማኅተም መኪናዎች ሳይኖሩ ከበግና ከፍየል ፤ ከፈረስም ቆዳ ሳይቀር ብራና ፍቀው ፣ ቀለማ ቀለማቱን ራሳቸው አዘጋጅተው ፣ የመቃብርዕ ቀርጸው ፣ በእጃቸው ጽፈው ፣ በእጃቸው ጠርዘውና ደጕሰው በአያያዝና በአቀማመጥ ጕስቍልና እንዳያገኛቸው ከላምና ከጥጃ ቆዳ ማሕደር ሰፍተውና አዘጋጅተው በመከባከብ ያቈዩአቸው መሆኑን ፣

ከላይ የተዘረዘሩትን የሃይማኖት የጸሎትና የሥነ ምግባር መጻሕፍት ማለትም ከጥንታዊው የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ከግዕዝ የተጻፉትን ወደ ልዩ ልዩ የብሔረ ሰብ ቋንቋዎችበመተርጐምና በማስተርጐም ማተሚያቤታችን በማተም ለአንባብያን በማቅረብ ላይ መሆኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቅ/ሲኖዶስምስለ ቅዱሳት መጻሕፍት መባዛት ከመቼውም ይልቅ ያሰበበት መሆኑን የኢትዮጵያጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ማይምነትን ከሀገሪቱ ለማጥፋት በአዘጋጀው ሰፊ የትም ሀርት ፕሮግራም ማ/ቤታችንም የፕሮግራሙ ተካፋይ በመሆን በሚሊዮን የሚቈጠሩ የማስተማሪያና የምንባብ መጻሕፍትን በማተም በሰፊው መተባበሩን ፤

እንደ አውሮፓ ዘመን አቈጣጠር ከ፲፱፻፳፱—፲፱፻፹ ዓ/ም በማ/ቤታችንየታተሙትንና በመታተም ላይ የሚገኙትንመ ጻሕፍትበ ዝርዝር ከመግለጻችንም በላይ ፤ በሴሚናሩ አዘጋጅዎች ጥያቄ መሠረት ከሰባት ያላነሱ መጻሕፍትን በማቅረብ አሳይተን ገንቢሂስ ተሰጥቶባቸዋል ብለዋል ። ሊቀ ካህናት ብርሃኑ መግለጫቸውን በመቀጠል በተለይም በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ፈቃድ ከተጻፈ ከአንድ መቶ ዓመት በላይ የሚሆን አንድ የብራና መጽሐፍ መዝሙረ ክርስቶስ በሴሚናሩ ላይ በማቅረብ ገለጻ ተደርጎ ስለነበር የኢትዮጵያ ን ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እጅግ በጣም ከማስመስገኑም በላይ በጠቅላላ የመጽሐፉ ዝግጅት ከፍያለ አድናቆትን ያተረፈናከዚህም ጋር የሴሚናሩ ተሳታፊዎች በፕሮግራም ተመድቦ በናይሮቢ ከተማ የሚገኙትን ማ/ቤቶች በክፍለ ሀገር ደረጃ በናኩሩ፣ በኬሪቶ ከተማዎች የሚገኙትን የሕትመት ቦታዎችን ተዘዋውሮ በመጐብኘትና በመመልከት ጠቃሚ ትምህርትን ያገኙ መሆኑን ገልጸዋል ።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ ጥንታዊትና ታሪካዊት እንደ መሆኗ መጠን በሚቻለው ሁሉ ድጋፍ መስጠት የሚያስፈልግ መሆኑን ከመግለጽ ጋር ፣ በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም በልዩ ልዩ አገሮች ያስተማሩአቸውና ያሰለጠኑአቸው ሰዎችእንዲሠሩ ከሰለጠኑበት ሥራ ላይ ከመነሣታቸውም በላይ ሪፖርት ሳይደረግላቸው በመቅረቱ ቅሬታቸውን መግለጣቸውንና በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳደር ለድጋፍእያመችም ይሉና ምክንያቱን ሲዘረዝሩ «በአንድ ሥራ ላይ ሠራተኛ ይመደብና ሥራውን ተለማምዶ ለመሥራት ሲሞክር ያላጠናውን ሌላውን የሚመድብ መሆኑን ፣ ከዚህም ጋር «የሂሳብ አያያዛቸው ዓለም አቀፋዊነት ስለሌለው ርዳታ ሰጪው ክፍል የርዳታው ገንዘብ ከምን ላይ እንደዋለና ምንስ ዓይነትውጤት እንዳስገኘ ትርፍና ኪሣራውንም ማሳወቅእስከ አልቻላችሁ ድረስ ርዳታ መስጠቱ፣ ወደፊትም መቀጠሉ የሚያስቸግር መሆኑን የሴሚናሩ አዘጋጆች ገልጸዋል በማለትሊቀ ካህናት ብርሃኑ መግለጫቸውን ደምድመዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ቤተ ክርስቲያን ለመልሶ ማቋቋሚያ ፩ ላንድሮቨሮች ረዳች

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስተዋሕዶቤተ ክርስቲያን በተፈጥሮና በሰውሠራሽ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖችን መርጃ የሚውል ግምታቸው ፩፻፷፭ ሺሕ ብር የኾኑ አምስት ላንድሮቨር መኪናዎች ለእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኰሚሽን ጳጕሜን ዐራት ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም አበረከተች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት የእርዳታ ሰጪ ድርጅት ያገኘቻቸውን ዐምስት ላንድሮቨር መኪናዎች ለጓድ ሽመልስ አዱኛ የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነርና የኢሠፓአኮ ማእከላዊ ኮሚቴ ዓባል ያስረከቡት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ናቸው ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በጽሕፈት ቤታቸው በተካሄደው በዚሁ የርክክብ ሥነ ሥርዓት ላይ ባደረጉት ንግግር ቤተ ክርስቲያን በአገራችን የደረሰውን የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋ ሁኔታ አጥንታ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ያገኘቻቸውን መኪናዎች ለኮሚሽኑ ስታበረክት ከፍተኛ ደስታ እንደሚሰማትና በቅርብ ጊዜም ውስጥ ሌሎች ርዳታዎች እንደሚደርሱ ገልጠዋል ።

ከዚህም ጋር እያይዘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከዚህ በፊት ለመልሶ መቋቋምና ለመሠረተ ትምህርት መርሐ ግብር የሚውል ሩብ ሚሊዮን ብር መርዳቷን አስረድተዋል ።

ጓድ ሽመልስ አዱኛ በበኩላቸው ቤተ ክርስቲያኗ ቀድሞም የድኵማን መጠለያና መርጃ ኾና መቈየቷን አስታውሰው በዕለቱ የተደረገው እርዳታ ይህንኑ ፅኑ ዓላማ የሚያድስና ጠቃሚ አገልግሎት የሚሰጥ በመኾኑ በተረጂው ሕዝብ ስም ምስጋናቸውን አቅርበዋል ።

ከዚህም ሌላ በዚሁ ወቅት በኢየሩሳሌም የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የአዋጡትን ሰባት ሺህ ያህል ብር ብፁዕ አቡነ ማትያስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ሊቀ ጳጳስ ለኮሚሽነር ሽመልስ አዱኛ አስረክበዋል ።

---

## ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የጀግኖች አምባን ጐበኙ፤ የገንዘብና የመጻሕፍት ርዳታ አደረጉ ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጳጕሜን ፫ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በደብረ ዘይት ከተማ በሚገኘው በቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በማስቀደስ ዐመታዊውን የቅዱስ ሩፋኤልን በዓል ለማክበር ለተሰበሰቡት ምእመናን አባታዊ ትምህርትና ቡራኬ ሰጥተዋል ።

በዚሁ ዕለት ደብረ ዘይት ውስጥ የሚገኘውን የጀግኖች አምባን ጐብኝተዋል ። ቅዱስነታቸው ከሥፍራው እንደ ደረሱ የጀግኖች አምባ አስተዳዳሪ ኰሎኔል ሙላት በላይ የክብር አቀባበል ካደረጉላቸው በኋላ ስለ ጀግኖች አምባ አቋምና ዓላማ ገለጣ አድርገውላቸዋል ። ከዚያም ቅዱስነታቸው ጐብኝታቸውን በመቀጠል የጀግኖች አምባ ትምህርት ቤቶችንና ልዩ ልዩ የማምረቻ ክፍሎችን እየተዘዋወሩ ከጐበኙ በኋላ ለናት አገራቸው ክብርና ህልውና ሲሉ ልዩ ልዩ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ጀግኖች የሚያበረታታና የሚያጽናና ምክር ከመስጠታቸውም በላይ ለዚሁም ድጋፍ የሚኾናቸው ስድስት መቶ መንፈሳዊ የመማሪያ መጻሕፍትና ብር ፩ሺ፬፻ (አንድ ሺህ አራት መቶ ብር) ርዳታ በማድረግ ቃለ ቡራኬ ሰጥተው ወደ በትረ ካናቸው ተመልሰዋል ።

ቅዱስነታቸው የጀግኖች አምባን በጐበኙበትና እርዳታውን ባደረጉበት ወቅት ብፁዕ አቡነ ሚካኤል ሊቀ ጳጳስ ፣ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ክፍለ ሀገር ጳጳስና ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የወለጋ ክፍለ ሀገር ጳጳስ ተገኝተዋል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የ፭ ላንድሮቨሮች ርዳታ ለጓድ ኮሚሽነር ሺመልስ አዱኛ ሲያስረክቡ ።




www.ethiopianorthodox.org

# በሕፃናት እስተዳደግ ጉባኤና በሰበካ አስተዳደር ጉባኤ የተደረጉ ሴሚናሮች

በሰበታ ጌቴሴማኒ ገዳምበሚገኘው የድርጅቱ ቅርንጫፍ ተቋም ሲካሄድ የሰነበተው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ያዘጋጀው ሴሚናር ነሐሴ ፲ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ተፈጽሟል ፣ ሴሚናሩ የተካሄደው ከሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ጀምሮ ለኻያሁለት ቀናት ያህል ሲኾን ለሴሚናሩ ተሳታፊዎች ሊቃነ ጳጳሳትና በቤተ ክርስቲያን ምሁራን የተሰጠ ሲኾን የጤና ጥበቃ ትምህርት ከየሆስፒታሉ በተጋ በዙ ዶክተሮች ፤ የአመጋገብ ትምህርት ከኢትዮጵያ ምግብ ጥናት ድርጅት ፣ የሳይኮሎጅ ትምህርት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፤ እንዲሁም ቻ ይ ል ድ ግሮዝ ማለት የሕፃናት አስተዳደግና አያያዝ ትምህርት ከሲዊዘርላንድ በተጋበዙ ሚስተር ፍሪስ በተባሉ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ የድርጅቱ መመሥረት የቤተ ክርስቲያን ዋና ዓላማ መኾኑን በመዘርዘር በዚህ ረገድ የሚታየው ርምጃ ሁሉ ደስ የሚያሰኝ መኾኑን ጠቅሰው ለየድርጅቱ ኃላፊዎች ማለት ለሴሚናሩ ተሳታፊዎች የሞራልድጋፍ ሰጥተዋል ።

ቀደም ሲል በሴሚናሩ መክፈቻም ወቅት የሕፃናት አስተዳደግ



የቤተ ክህነት ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስኪያጅ በደሴ ከተማ በሚገኘው አቡነ ጴጥሮስ የሕፃናት ማሣደጊያ ት/ ቤት የሚገኙትን ሕፃናት በጎበኙበት ወቅት ።

ማለት ለየክፍለ ሀገሩ አዳሪ ት/ቤት ዲሬክተሮችና ሞግዚቶች ልዩ ልዩ ትምህርቶች የተሰጡ መሆናቸውን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ አቶ ጸጋዬ በርሄ ገልጸዋል

ከቀረቡትም የትምህርትዓ ይነቶች መንፈሳዊ ትምህርት በብፁዓን እንግዳ ምሁር በሰፊው የተሰጠ መኾኑን አቶ ጸጋዬ ጨምረው ገልጸዋል።

ሴሚናሩ የተከፈተው በብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጸሎተ ቡራኬና የማበረታቻ ምክር ሲኾን በተዘጋበትም ወቅት አቶ ...ርስዔ ኀዘን አበበ የጠቅላይ ቤተ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ አቶ ጸጋየ በርሄ ስለሴሚናሩየትምህርት ይዘትና ጠቃሚነት በጠቅላላው ስለ ድርጅቱ ዓላማና የሥራ አቋም በማብራራት ገለጸ አድርገዋል ።

በሴሚናሩ ፍጻሜ ወቅት ከፍተኛ የሥራ ውጤት ላሳዩ አዳሪ ት/ ቤቶ




ች በተሰጠው ደረጃ (ግዕረግ) መሠረት የሐረር ኖሕተ ምሥራቅ የሕጻናት ማሳደጊያ የአዳሪ ት/ቤት በአንደኛ ደረጃ ስለወጣ ድርጅቱ የዓመቱ ድርጅት ፤ ሕጻናቱም የዓመቱ ሕጻናት ፤ የድር ጅቱም ሥራ አስኪያጅ የዓመቱ ሰው መበላቸውንና ከዚህም በማያያዝ በሁለተኛ ደረጃ የወጣው የጎንደር ሐዋርያው ጳውሎስ የሕጻናት ማሳደጊያ ተቋም እንደሚገኙ አቶ ጸጋየ ጠቅሰው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕጻናት አስተዳደግ ጉባኤ በጠቅላላው በዘጠኝ ክፍላተ ሀገር አራት ሺህ ሁለት መቶ (፬ሺ፪፻) ዕጓለ ማውታ የሆኑ ሕጻናት እንደሚያሳድግ በመግለጽ የድርጅቱ ዋና ዓላማ ረዳት ያጡትን ሕጻናት በመንፈስ ፤ በአእምሮና በአካል ተንከባክቦ ማሳደግ ዋዕት እንደምትሆን በገለጹላቸው መሠረት ሚስተር ሉደር ሉወርስም በበኩላቸው ለስድስት መቶ ተጨማሪ ሕጻናት በጀት ፈቅደዋል፤ለወደፊቱም በቤተ ክርስቲያኗ በኩል ለሕጻናት የሚደረገው ርዳታ እንደ ችግሩ መጠን እየታየ ልግሥናቸውን እንደሚቀጥሉ ቃል ገብተዋል ሲሉ መግለጫቸውን ደምድመዋል ።



እቶ ሲሳይ ኃይለ ሚካኤል
የኖሕተ ምሥራቅ ት/ቤት የሥራ መሪ

ጸጆት ሪታና ቤተሰቡ
ምግፀ ቤተ መጻሕፍት



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ሥር ሚገኙት የአዳሪ ት፣ ቤቶች ዲሬክተሮች በሴሚናርና ላይ።

ሲሆን በሦስተኛ ደረጃ የወጣው ደግሞ የዐድዋ ፈለገ ሕይወት የሕጻናት ማሳደጊያ ተቋም መሆናቸውን አቶ ጸጋዬ አስረድተዋል ።

የሐረር የሕጻናት ማሳደጊያ አዳሪትምህርት ቤት የተመሠረተው በክፍለ ሀገሩ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ አቡነ አብርሃም አማካይነት በሠላሳ ሕጻናት ብቻ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ባደረገው ከፍተኛ ጥረት መቶ አርባ (፻፵) ሕጻናት መሆኑን አቶ ጸጋየ አብራርተዋል ።


አቶ ጸጋዬ በሰጡት የመጨረሻ መግለጫ ሚስተር ሉደር ሉወርስ (ሉርስ)የተባሉት ጀርመናዊው የዚሁ ድርጅት ርዳታ ሰጪ ድርጅት ኃላፊ ባለፈው ጥር ወር ኢትዮጵያ መጥተው በነበረበት ጊዜ ከብፁዕ ወቅዱስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ጋር በመነጋገር ቅዱስነታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለሕጻናት ከብካቤ የተቻላትን ያህል መሥ



www.ethiopianorthodox.org

## በአሥመራ ከተማ በክፍለ ሀገር ደረጃ የሰበካ ጉባኤ ሰሚናር ተደረገ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በሰበካ ጉባኤ መምሪያና በወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ትብብር ተዘጋጅቶ በአሥመራ ከተማ በፍኖተ ብርሃን ማኅበር መንእሰይ አዳራሽ በክፍለ ሀገር ደረጃ ከነሐሴ ፳ እስከ ነሐሴ ፳፭ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓም ድረስ ሰሚናር ተካሂዶአል ።



በአሥመራ ከተማ የተደረገው የሰበካ ጉባኤ ሴሚናር

ሰሚናሩ በብፁዕ አቡነ መርሐ ክርስቶስ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ መሪነት ሥርዓተ ጸሎት ተደርጎ ሲከፈት የክፍለ ሀገሩ አስተዳደር ተወካይ አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረ መድኅን ተገኝተዋል ። በዚሁም ወቅት አቶ ኃይለ ሚካኤል ገብረ መድኅን ስለሰሚናሩ አጭር ንግግር አድርገዋል ። የሰሚናሩ ፣ ተሳታፊዎች ከገዳማት ፣ ከአድባራትና ከገጠር አብያተ ክርስቲያናት የተወከሉ አስተዳዳሪዎች ምእመናን የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት ዓባሎች ሲሆኑ እነዚህም በጊዜው ከሰሚናሩ ተገኝተው ለመሳተፍ እንዲችሉ የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳር መኪና የሚገባበትን በመኪና ፣ መኪና የማይገባበትን በአእሮፕላን በማጓጓዝ የረዳ መሆኑን ከሰሚናሩ ተገልጾአል ስለዚሁ መልካም ትብብሩም መልእክተኞቹና የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ከልብ አመስግኖአል ።

የሰሚናሩ ዋና ዓላማ የሰበካ ጉባኤን ለማቋቋምና ለማጠናከር እንዲሁም ስለሰበካ ጉባኤ ማቋቋምና አፈጻጸም ተሻሽሎ የወጣውን ቃለ ዓዋዲ ተግባራዊ ለማድረግ በሌላ በኩል ደግሞ ለሥራው ቅልጥፍና የሚረዳው ዋና መንገድ ማዕከላዊ አሠራር ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ መንበረ ጵጵስናው ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ከዚያም እስከ መንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ድረስ ሲዘረጋ በመሆኑ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ፣

ተከታዩን በ፳፯ኛ ገጽ ይመልከቱ



## መስቀልና ታሪካዊ አመጣጡ ።

የአይሁድን ዐድማ በመጨረሻ ያፈረሰ ክቡር መስቀሉ ነው ፤ ጌታ በንጹሕ ደሙ ያከበረው የአጋንንት የአይሁድ ድል መነሻ ያደረገው መስቀሉ ፣ ጌታ ካረገ ጀምሮ ልዩ ልዩ ተአምራትን ያደርግ ነበር ።

አጋንንትን ያባርራቸው ድውያንን ይፈውሳቸው ነበር ። ይህ ተአምራትን አድራጊነቱ አይሁድን በጣም አስቈጣቸው ።

በየደጃቸውና በየዙሪያቸው የሚገኘውን ጉድፍ በላዩ እያፈሰሱ እንዲቀብሩት ዐዋጅ አወጡ ፤ ከሁለት መቶ በበለጠ ዘመን ጉድፍ ፣ አፈርና ጠጠር በማፍሰስ ደፈኑት ።

ይህንን ማድረጋቸው የክርስቶስ እምላክነት እንዳይታወቅባቸው ነው ፣ የፈጣሪን ኃይል ፍጡር ሊገታው ሊያግደው ሊወስነው አይችልምና እግዚአብሔር ያደረባት ዕሌኒ ክቡር መስቀሉን ለመፈለግ ተነሣች ፣ ልጅዋ ቈስጠንጢኖስም በገንዘብም በሠራዊትም ጉልበት ረዳት ሱባዔ ገብታ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመልክታ የተቀበረበት ቦታ እንደ ታላቅ ኮረብታ ከኾነ በኋላ ክቡር መስቀሉን ለማግኘትና ለማውጣት ቻለች ። የመገኘቱንም የምሥራች ለልጅዋ ለቈስጠንጢኖስና ለዓለም ክርስቲያን አሰማች የመገኘቱን የምሥራች በመጀመሪያ ከሰሙት አህጉር እንዷ ኢትዮጵያ ናት ይኸው ይታወቅ ዘንድ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዚያ ጊዜ ጀምራ የሕፃናትን ስመ ክርስትና ገብረ መስቀል ብርሃነ መስቀል እያለች በመስቀል ስም እየሰየመች ለክቡር መስቀሉ መስገድን እያስተማረች ኖራለች ፣ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ መጽሐፈ ምሥጢር በተባለ መጽሐፋቸው ክቡር መስቀሉ በኢትዮጵያ እጅግ ተወዳጅነት እንደነበረ ሲያስረዱ የሕጽዋ ለህንደኬን ስብከት በሰሙ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ወንዶችና ሴቶች በየግንባራቸው በየገጻቸው በየራሳቸው በየልብሳቸው ትእምርተ መስቀልን መቅረጽ የማሠር ጀመሩ ብለዋል ።

ይህ ሥርዐት ተያይዞ እስከ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ ዘመነ መንግሥት ድረስ ቈየ በዚህ ጊዜ የግብጹ ገዢ አባ ሚካኤል የሚባለውን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያንን ፓትርያርክ ማሠሩንና በጭቆና ማጋዙን ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሰሙና አዘኑ ተከዙ ።

ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት የሚል ዐዋጅ ተነግሮ የዘመቻ እንቅስቃሴ በተደረገ ጊዜ የግብጽ ግዛት ወኪል ለበላዩ ባለ ሥልጣን የዘመቻውን ዜና አስታወቀ የግብጽ ጠቅላይ ገዥ አባ ሚካኤልን በዚህ ምክንያት ከእሥራቱ ፈታው ከግዞቱ ቤት አወጣው ።

አባ ሚካኤልንና ሌሎቹንም ታሥረው የነበሩትን የግብጽ ክርስቲያኖች ፈትቼልሀለሁ ወደ አገርህ ተመለስልኝ ዳግመኛ አባ ሚካኤልንም ክርስቲያኖቹንም አልነካብህም የሚል ኪቃል ኪዳን ያላነሰ ጽኑ ቃለ መልዕክት ወደ ዐፄ ሰይፈ አርዕድ አስተላለፈ ።

ይህ ቃል እስከ ዐፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት ጸንቶ ከኖረ ኋላ የዐፄ ሰይፈ አርዕድን መሞት ቢሰማ አባ ሚካኤልንና የእስክንድርያን ክርስቲያኖች እንደ ገና አሠራቸው አጋዛቸው ፣ ምክንያቱም የገጸ በረከት ገንዘባችሁን ገብሩልኝ በማለት ነው ይባላል ።

በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰፍቶ ተደራጅቶ ነበርና በግብጽ ክርስቲያኖች ላይ የተደረገው ጭቆና ዐፄ ዳዊትን በጣም አስቈጣ እኔስ ከአባቴ አንሳለሁን ስለዘብለው የጦር ሠራዊታቸውን ለዘመቻ አደራጁ የኢትዮጵያና የግብጽ ግዛት ድንበር ሆኖ ወደ ነበረው አስዋን ወደ ተባለው ሥፍራ ዘመቱ ግብጽ ስትጠቀምበት የኖረውን የዐባይን ውሃ ለመገደብ ዝግጅት አደረጉ በአስዋን አቅራቢያ የነበረው የግብጽ ግዛት ወኪል የኢትዮጵያ መንግሥት ሊወጋን መጣ ብሎ መልእክት ወደ ግብጽ ባለ ሥልጣን አስተላለፈ ።

የግብጽ ባለሥልጣን አባ ሚካኤልንና ክርስቲያኖቹን ፈታና አሥራ ሁለት ዕልፍ ወቄት ወርቅ አሲዞ ወደ ኢትዮጵያ ላካቸው የኢትዮጵያ ንጉሥ ዐፄ ዳዊትም ይቅርታ አድርጎ እንዲመለስልኝ ለምኑልኝ የሚልበት ቃል ነገርዋቸው ነበር ።

ዐፄ ዳዊት ከሥጋዊ ብልጽግና መንፈሳዊ ብልጽግናን የሚመርጡ ነበሩና ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ያዳነው በክቡር ደሙ ነው እንጂ በወርቅ በብር በዕንቍ ዓለምን አላዳነውምና ያመጣችሁትን ዐሥራ ሁለት ዕልፍ ወቄት ወርቅ አልቀበልም መልሳችሁ ውሰዱ አኗቸው አገሬን ኢትዮጵያን ዐባር ቸነፈር ያማታታል አደጋ ይጥልባታል የአጋንንት ጦር ይነሣባታልና የጌታዬን መስቀል ላኩልኝ ብለው አሰናበቷቸው ይህንን ቢነግሩት የግብጽ ባለሥልጣን ያሠጋው የውሃ መገደብ ነበርና በእሳቡ ተስማማ ከጌታ መስቀል ግማድ የተባለውን የቀኙን ክፍልና ልዩ ልዩ ንዋያተ ቤተክርስቲያንን አሲዞ እንደገና ላካቸው « ዐፄ ዳዊትም አስዋን ድረስ ሄደው መስከረም ፲ ቀን ክቡር መስቀሉን ብዙ ሠራዊትንና ካህናትን አሰልፈው ተቀበሉ የቀድሞ ሊቃውንት ስለ አቀባበሉ ታላቅነት የደረሱት ዐርኬ እንዲህ ይላል ሰላም እብል ዕፀ አድኅኖ መስቀለ በዛቲ ዕለት በኢትዮጵያ ተተክለ ፣ ዳዊት ፣ ወሕዝቡ እንዘ ይገብሩ መድበለ ፣ እምጣነ ረከቡ ከመ ልቦሙ ሰአለ ፣ በቃለ ትፍሥሕት ደምፁ ወገብሩ በዐለ ። ዐፄ ዳዊት በዚያ ጊዜ በዕልፍ የሚቈጠር ፍሪዳ በግ ፍየል አዘጋጅተው ማለት ፍሪዳ እረዱ ጠጅ አውርዱ ብለው ብዙ ተድላ ደስታ አድርገዋል አስደርገዋል ብሎ መጽሐፈ




www.ethiopianorthodox.org

ታሪክ ይመሰክራል ሊቃውንቱና ካህናቱ አጽንቶ ሕዝበ መሃይምናን፣ ብቤተ መርኅ ተመልዑ ክርስቲያን ብለው በዘመሩ ጊዜ እጅግ ደስ ብሏቸው ብዙ ሽልማት ለካህናት ሰጥተዋል ሊቃውንት የደጋማ ሰዎችን ወረታ አያስቀሩምና በመጀመሪያ ክቡር መስቀሉን በማስፈለግ ለረዳ ለቈስጠንጢኖስ በድርሰታቸው የሰጡት መታሰቢያ እንዲህ የሚል ነው ።

መስቀል የድል መንግት ምልክት ነው አይሁድና አጋንንት ድል ተነሥተው በታልና መስቀል የደስታ የክብር ምልክት ነው ምእመናን ከአጋንንት ቁራኝነት ተላቀው ደስታ ክብር ተሰምቶአቸዋልና ዐፄ ዳዊት በአስዋን ላይ ክቡር መስቀሉን መስከረም ፲ ቀን ተቀብለው ሥርዐተ በዐሉን ከአስከበሩ በኋላ ስናር የተባለው ክፍለ ሀገር በእርሳቸው ግዛት የሚመራ ነበር

ንጉሥታቸው እስኪተኩ ድረስ ክቡር መስቀሉ ጠስናር ቈዩ ። ግዛቱ ግን ወደ መሐመድ ተከታዮች እጅ ገብቶ ነበር ለቈስጠንጢኖስ የመስቀሉ ክብር በእራእይ እንደ ተገለጠለት ለዐፄ ዘርዐያዕቆብም በራእይ ተገለጸላቸው ራእያቸው «አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል» የሚል ነበር ።

የዚህን ራእይ ትርጓሜና ምሥጢር ከሊቃውንት ጠየቁ ፤ ሊቃውንቱ



ሰላም እብል ቈስጠንጢኖስሃ ኅሣሤ መስቀለ እሐዱ አምላክ ወቅድስት ሥላሴ ርትዐ ክርሥ ሚካኤል እንተ ትሴሰይ ቅዳሴ፣ ኢንፍራህ እጽንዐነእምገርግ ግሩም ነሐሴ ከመ ግርማ ፈርኦን ፈርሁ እሥራኤል ወሙሴ ።

ርና ከአበዋን ወደ ስናር በክብር አስወስደው በእልፍኛቸው አጠገብ መቃኞ አሠርተው ቀሳውስት እያጠኑ ካህናት ጸሎት እያደረሱ የአገልግሎት ሥርዐት እንዲፈጽሙ አደረጉ ፣

ልጃቸው ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ በመ

ም አባትዎ ዐፄ ዳዊት ያስመጡት ግማደ መስቀል በስናር ይገኛል፣አስመጥተኸ በመስቀለኛ ሥፍራ አኑረው ሲልዎ ነው አሏቸው፣ የስናር ግዛት በሌሎች እጅ ከገባ ብለው ከተት ሠራዊት ፤ ምታነጋሪት ብለው የጦርነት ዐዋጅ አሳወጁ የግብጽ



መንግሥትም በኃይል መነሣታቸውን ሰምቶ የአባትኸን ዕቃ ውሰድ እኔንና አንተን ምንም የሚያዋጋን ነገር የለም የሚል የሰላም ቃል አስተላለፈላቸው ፤ በዚህ ተስማሙ በብዙ ዕልፍ የሚቈጠር ሠራዊታቸውን በመቶ የሚቆጠሩ መሳፍንትን መኳንንትን ሊቃውንትንና ካህናትን አስከትለው ክቡር መስቀሉን ከስናር በክብር አስነሥተው ወደ ግሼን አስመጡ ።

መስቀለኛ ሥፍራ ለማግኘት አንድ ዐመት ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ከተራራ ወደተራራ መዘዋወራቸውን መጽሐፈ ታሪክ መልካም አድርጎ ልጦታል ጤፉት የተባለችው መጽሐፍም በሚያስተማምን አነጋገር አ ብራርታዋለች እርሳቸው ዐጼ ዘርዐ ያዕቆብም ያድከዋ ለደብረ ከርቤ ወረከብከዋ ከመበአማን ትእምርተ መስቀል ይእቲ ማለት ደብረ ከርቤን ተዘዋውሬ አየኋት የመስቀል አምሳያነት እንደ አለባት ዐወቅኹ ማለታቸው በዚችው ጤፉት በተባለችው መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሶአል ።

ደብረ ከርቤን ዙረው አይተው ተመልከተው ከመኳንንቶቻቸውና ከሊቃውንቶቻቸው ጋር ምክር አደረጉ እነርሱም በዚች ተራራ ላይ አኑረው ሲልዎ ነው ብለው ተራራዋንና ራእያቸውን አነጻጽረው አመሳስለው አስተያየት አቀረቡላቸው፤ በዚሁ ምክር ተስማምተው መስከረም ፳፩ ቀን ክቡር መስቀሉን በደብረ ከርቤ አናት መሬቱን አጥልቀው አስቈፍረው እንደ አስኖሩት ጤፉት ስታስረዳ የሣጥኑን ዐይነት በዝርዝር ትናገራለች እንዲህም ትላለች የወርቅ ሣጥን — የብር ሣጥን —የኒኬል ሣጥን — የመዳብ ሣጥን—የብረት ሣጥን ፤ ይህ አቈጣጠር ከታች ወደ ላይ ነውና ጠንቅቆ መመልከት ያሻል ፤ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብም ወበፍጻሜሁ አግበርኩ ሣጹነ ዘኀፂን ማለት በመጨረሻው ወደ አፈሩ አጠገብ ያለውን ሣጥን የብረት አደረግሁት ብለዋል ፣ ዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ጻድቅ ደግ

እንደ መሆናቸው መጠን በዚችውበደብረ ከርቤ ላይ ብዙ ተአምራታዊ ሥራ እንደ ተፈጸመላቸው ጤፉት አንድ በአንድ ዘርዝራ ትናገራለች ። ጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤልም ይህችን ደብረ ከርቤን የተሳለመ ቅድስት ኢየሩሳምን እንደ ተሳለመ ይቈጠርለታል ብለዋል ። እንዲህም ማለት ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ተሳል ምየሚያገኘውን በረከትና ጸጋ ክብር ደብረ ከርቤን ። ተሳልሞ ያገኘዋል ማለት ነው ይህንንም የሚያስገኝ የሃይማኖት ጽናት ነው ማለት ክቡር መስቀሉ ከመናፍስት ርኩሳን ከአጋንንት ጦር ያድነኛል ይታደገኛል ብሎ ከተማጠነበት ካመነበት በኃይለ መስቀሉ ከፈተናው ሁሉ ይጠበቃል፤በዐራቱመዐዝናት ያለ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ከቀድሞ ተያይዞ የመጣለትን ሥርዓተ በዓል መሠረት አድርጎ በያመቱ መስከረም ፳፩ ቀን በግሸን ተራራ ላይ እየተሰበሰበ በረከተ መስቀሉን ይሳተፋል ጸሎተ ንስሐን እያደረሰ ሥጋውን ደሙን ይቀበላል ።

ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ክቡር መስቀሉን በክብር በአኖሩ ጊዜ የእግዚአብሔር አብን ቤተ ክርስቲያን ሠሩ፤ዕሴኒ የተባለችው እኅታቸውም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ቤተ ክርስቲያን አሳንጸ ነበርና የመስከረም ኻያ አንድ ቀን በዐለ ማርያምን በብዙ ሺህ የሚቈጠር ሕዝብ ተሰብስቦ ያከብረዋል።

የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ሥርዐት ከጥንት ተያይዞ መምጣቱ በዚህ ይታወቃል ። ጌታ እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን በብሥራተ ቅዱስ መል አክ እንዲሁም በዕንሱ በልደቱ በስቅለቱ እንደ አከበራት እናከብራታለን እንሰግድላታለን ።

ቅዱስ መስቀሉንም በንጹሕ በክቡር ደሙ እንደ አከበረው እናከብረዋለን እንሰግድለታለን እንሳለመዋለንም፤ መናፍቃን ግን መስቀሉን መጀመሪያ በኢየሩሳሌም፤ዳግመኛ በፋርስቢቀብሩትናቢሠውሩት እንደተቀበረ እንደ ተሠወረ አልቀረም ተነሥቶ ልዩ ልዩተአምራት



እያደረገ የክርስቶስን አምላክነት መሰከረ እንጂ በዐመት የሦስት በዐላት አከባበር ይደረግለታል። መስከረም ፲፮ ቀን በደመራ የሚከበረው ዕሌኒ የዕንጨቶች ደመራ አስደርጋ የመስቀሉን ሥፍራ ያገኘችበት የተቀበረበ ትን ቅዱስ መካን ማስቈፈር ያስጀመረችበት ኋላም በቅዱሳት መካናት ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጸ ቅዳሴ ቤታቸ[illegible]ን ያደረገችበት ነው ።

በማግሥቱ መስከረም ፲፯ ቀን



አፈ ሊቅ አክሊሉ ገብረ ኪሮስ

ዐቢይ በዐሉ የሚከበርበት ነው መጀመሪያ የተገኘው መጋቢት ፲ ቀን ሲሆን ታሪኩ በመጋቢት ፲ ቀን መተረኩና መወሳቱ ሳይቀር በለውጡ መስከረም ፲፯ ቀን በብዙ ሕዝብ ሰልፍና በብዙ ድርጅት እንዲከበር የወሰኑ ሊቃውንት ናቸው ።

አፈሊቅ አክሊሉ ገ/ ኪሮስ

## ተአምራታዊ ዜናዎች

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ከአሥሩ አንዱ ብቻ ጌታችንን ለማመስገን ወደ እርሱ ሲመጣ ዘጠኙ ግን ከነጻን ምን ያደርግልናል ብለው ወደ የፈለጉበት ሄዱ እንደዚሁም ሁሉ በዘመናችንም በእግዚአብሔር ቸርነት በቅዱሳን አማላጅነት ሲነጹ በኃይላቸው እንደነጹ እየቈጠሩ ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ሳይሰጡ ይቀራሉ ሉቃስ ፲፯፣፲፩—፱፲ ።

ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም

www.ethiopianorthodox.org

# ተአምራታዊ ዜናዎች

አዲስ አበባ በሚገኘው በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖትቤተ ክርስቲያን ከየካቲት ፫ ቀን እስከ ሐምሌ ፴ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ድረስ ፳፻፸፱ ሕሙማን በጠበል የተፈወሱ መሆናቸውን የደብሩ አስተዳዳሪ መምህር ዘካርያስ ኃይሉ ማርያም ገለጡ መምህር ዘካርያስ ይህ የተቀደሰ አገልግሎት እንዴት እንደ ተጀመረና ተአምራቱም እንዴት እንደተገለጠ ጠይቀናቸው ሲያስረዱን የተጀመረውና ተአምራት የታየውም



አባ ዘካርያስ ኃይሉ ማርያም የደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ

ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ወር ነው ይህን ሥራ በማከናውንበት ጊዜም አባ ገብረ መድኅን ተስፋዬና ቀሲስ ኪሮስ ያተባሉ ሁለት መናንያን የደብሩ አገልጋይ ከሆኑ ከአባ ታደሰ ደረሰ ጋር የጻድቁን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ገድልና ወንጌሉን በማንበብና ሌላውንም ጸሎት በማድረስ እየረዱኝ ብዙ ገቢረ ተአምራት ከታየ በኋላ ከግንቦት ፩ ቀን ፸፪ ዓ/ም ጀምሮ ካህናቱ ሥራውን ተረክበው ሥርዓተ ጸሎቱን በማከናወንና በማጥመቅ በሚፈጽሙት መንፈሳዊ አገልግሎት ከላይ የተጠቀሱት ሕሙማን ከልዩ ልዩ ደዌ ለመፈወስ ችለዋል ።

ይህ የተቀደሰ አገልግሎት ከተጀመረ ጀምሮ ሕሙማን በከባድ ደዌ ተይዘው ሲሠቃዩ ከኖሩ በኋላ በዚሁ ጠበል አማካይነት ለመዳን የበቁና በቃላቸው ምስክርነት የሰጡ ፭፻፳፱ ሲሆኑ እነዚህ ሕሙማን ከደዌአቸው ተላቀው ወደየተግባራቸው ተመልሰዋል ካሉ በኋላ አሁንም ጸሎቱ የሚከናወንበትና ሕሙማን የሚጠመቁበት ከምዕመናን በተወጣጣ ብር ፪ሺ፯፻፹ ሁለትሺህ ሰባት መቶ ሰማንያ ብር በታደሰው አዳራሽ ውስጥ ሲሆን ተጨማሪ ከፍተኛ አዳራሽ የሚያስፈልግ መሆኑን ምዕመናን እምነውበት ኅብረታቸውን በማጠናከር ላይ ይገኛሉ ብለዋል ንግግራቸውን በመቀጠል በተለይም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፱፻፸፪ዓ/ም ከሕሙማኑ መካከል ተገኝተው ጸሎተ ቡራኬውን ካደረሱ በኋላ ሰፋ ያለ ትምህርተ ወንጌል በመስጠት ፲፪ ዓመት ሙሉ ደም ይፈሳት የነበረችውንና ፲፰ ዓመት በሰይጣን ቁራኛ ተይዛ የነበረችውን ከወንጌሉ ጠቅሰው ለሕሙማኑ ካብራሩ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖትሽ አዳነሽ ሃይማኖትህ አዳነህ እያለ ይፈውሳቸው እንደ ነበር ገልጸው እምነት የመጣ ሁሉ እንደ ሚድን የሃይማኖትን ጠቃሚነት አረጋግጠው ሕሙማ



አቶ መብራቱ በላይ

ኑን አጽናንተዋል ፣ ለካህናቱም የሐዋርያት ተግባር ምን እንደ ነበር አስገንዝበው በጀመሩት ሐዋርያዊ ተግባር ተግተው እንዲገፉበት ሰፋ ያለ መመሪያና አባታዊ ቡራኬ ሰጥተው በመሄዳቸው በሕሙማኑና በደብሩ ካህናት ላይ ታላቅ ደስታ ሆኖ አል ሲሉ አስረድተዋል ።

ከተፈወሱት ሕሙማን መካከል አንዳንዶቹን አነጋግረን ስለ ሕመማቸውና አሁን በእግዚአብሔር ኃይል ስላገኙት ደህንነት የሰጡንን አስተያየት ከዚህ በታች በቅደም ተከተል እንገልጻለን ። በመጀመሪያ አቶ መብራቱ በላይ አድራሻቸው ጎንደር ክፍለ ሀገር ሊቦ አውራጃ አዲስ ዘመን ከተማ ቀበሌ ዜሮ አንድ ሥራቸው የሁለተኛ



አቶ ተፈራ ሙሴ

ደረጃ ት/ቤት መምህር ሲናገሩ እኔ በደረሰብኝ ድንገተኛ የአእምሮ መታወክ ወይም ራስን መሳት በጎንደር ከተማ የጤና አጠባበቅ ኮሌጅ ሆስፒታል ምርመራ አድርጎልኝ ነበር ነገር ግን በሽታውን ሊረዳው ስላልቻለ ወደ አዲስ አበባ ለከፍተኛ ሕክምና ላከኝ በአዲስ አበባ ካሉት ሆስፒታሎች ወደ አማኑኤል ተልኬ ከተመረመርኩ በኋላ እንድ ተኛና ገንዘብ እንድከፍል ተነገረኝ ይሁን እንጂ የገንዘብ እጥረት ስለነበረብኝ መድኃኒቱን እየገዛሁ በውጭ ስታከም ፈጽሞ ሳይሻለኝ ቀረ በሕክምና በኩል ያለኝ ተስፋ የመነመነ ሆኖ ካገኘሁት በኋላ ወደ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መጥቼ ለ፲ ቀናት ያህል እንደ ተጠመቅሁ በእግዚአብሔር ተአምር ሠሪነት ፈጽሞ ጤንነቴን አግኝቼ ድኛለሁ እጅና እግሬን በእግር ብረት ታስሬ ሁለት ወር ሙሉ አእምሮየን ስቼ በመጮህና በመንገላታት ብዙ ስቃይና መከራ ከደረሰብኝ በኋላ በጠበሉ ተጠምቄ ደህንነትን ለማግኘት በመብቃቴ ቸርነቱ የማያልቅበት እግዚአብሔርን እያመሰገንኩ ሙሉ በሙሉ ለመዳኔ የምስክርነት ቃሌን በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ላረጋግጥ እወዳለሁ በማለት አስተያየታቸውን ደምድመዋል ።



፪ኛ/ አቶ ተፈራ ሙሴ በሐረርጌ ክፍለ ሀገር ጩርጩር አጋጉ አዉራጃ ከርባ ቦርደዴ በቀበሌ ዜሮ አንድ ነዋሪና የምድር ባቡር ኩባንያ ሠራተኛ ከዚህ እንደ ሚከተለው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል ባደረብኝ የልክፍት በሽታ አእምሮዬን አጥቼ ስሰቃይ ከቆየሁ በኋላ ድሬዳዋ ወደ ሚገኘው የፈረንሳይ ሆስፒታል ዘመዶቼ ወስደውኝ ለሁለት ቀናት ያህል ሐኪም ሲመረምረኝ ቆየ ነገር ግን ዶክተሩ በሽታዬ ምን እንደሆነ ሊረዳው ካለመቻሉ የተነሣ ከአቅሜ በላይ ነው ብሎ አዲስ አበባ ወደ ሚገኘው አማኑኤል ሆስፒቲታል ጽፎልኝ ዘመዶቼ ይዘውኝ መጡ ።

አዲስ አበባ እንደ ደረስን ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ከመድረሳችን በፊት በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት በሚካሄደው መንፈሳዊ ተግባር የልዩ ልዩ ሕሙማን መዳን መስፋፋቱን ስለሰማን በቀጥታ ወደዚሁ ቤተ ክስርቲያን መጥተን እቅጽሩ እንደ ደረስንና ገድሉ ሲነበብ እንደሰማን ያደረብኝ ርኩስ መንፈስ በኃይል እያስጮኸ አስለፈለፈኝ አሉኝ ዘመዶቼ እንደገናም ለአራት ቀናት ያህል መላልሸ ከደብሩ በምመጣበትና በምጠመቅበት ጊዜ እንደ መጀመሪያው ያስጮኸኝና ያስለፈልፈኝ ነበር በመጨረሻ ግን ርኩሳን መናፍስቱ በእግዚአብሔር ቃል ተቃጥለው ስለጠፉልኝ አእምሮዬ ተመልሶልኝ ፍጹም ደህንነትን አግኝቻለሁ ።



አቶ ሐሰን መሐመድ

ስለዚህ እኔን ደስ እንዳለኝ ወገኖቼን ማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ ደስ ይበላቸውእላለሁ ከእኔ ጋር እንደ እኔ ሁናችሁ የተክለ ሃይማኖትን አምላክ ልዑል እግዚአብሔርን በታላቅ መንፈሳዊ ስሜት እንድታመሰግኑልኝ በትሕትና አሳስባችኋለሁ ሲሉ መልእክታቸውን ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው አስተላልፈዋል ።

፫ኛ/ ሐሰን መሐመድ አድራሻቸው ባሕር ዳር ከተማ የ፲፪ኛ ክፍል ትምህርቱን አጠናቆ ከጨረሰ በኋላ ከመንግሥት ወደ ተምሮ ማስተማር ሊላክ ይጠራል ከዚያም የሚሄድበት ሰዓት ተነግሮት ምሳውን በልቶ ወደ ሚንቀሳቀስበት ሥፍራ በብስክሌት ሲበር ከመኪና ጋር ተጋጭቶ ራሱ ተፈንክቶ ደሙ ሲፈስ በዚያው ይለከፋል ምንም እንኳ ቁስሉ ቶሎ ቢድንም በልክፍቱ ምክንያት እንጉሉ ይዛባል በባሕር ዳርም ሆነ በአዲስ አበባ ካሉት ሆስፒታሎች ሕክምና ሲያደርግ ትንሽ ተሻለውና ወደ ሀገሩ ሄዶ እንደገናም ሕመሙ ተነሣበት አእምሮውን እስኪስት ድረስ ታመመ በሰንሰለት ታስሮም አዲስ አበባ ወደ ሚገኘው ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ለህክምና ተላከ ጥቁር አንበሳ ስላልቻለም ወደ አማኑኤል ሆስፒታል ላከው የአማኑኤልሆስፒታል ደግሞ የአእምሮ ጭንቀት እንጂ ደህና ነው ብሎ መለሰው ።

ከዚህ በኋላ ብዙ ችግርና እንግልት የደረሰባቸው አባትየው በሰው በኩል የሚጠብቁት እርዳታ ሁሉ እስከምን ድረስ እንደሆነ ተገነዘቡት ታላቅ የሕክምና ሥፍራዎችን ሁሉ አዳርሰዋል ነገር ግን ልጃቸው ተፈውሶ ጤንነት ሊያገኝ አልቻለም የእርሳቸው መውጣት መውረድምመንገላታትና መድከምም መድኅን አልተገኘለትም አሁን አንድ ታላቅ ሐኪም ቤት እንደ ቀረባቸው አስተዋሉ እርሱም ወደ ታላቁ ሐኪም ወደ እግዚአብሔር ቤት መሄድ ነው ።

ስለዚህ በሰው ጥበብ በሰው መድኃኒት ሊድን ያልቻለ ልጃቸውን ይዘው ወደ ደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሄዱ በዚያም ሐሰን እጁና እግሩ እንደታሠረ በእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ሲጠመቅ የያዘው ጋኔን ከመኪና ጋር ሲጋጭ ነው የለከፍኩት ሲል ተናገሮ በአምስተኛው ቀን ስለለቀቀው ሙሉ ጤንነት አግኝቶ ፈጣሪውን አመስግኖ በሰላም ወደ ሀገሩ ሊመለስ መቻሉ ተገልጿል ።

፬ኛ/ አቶ ንዋይ ገብረ ማርያም ነዋሪነታቸው አዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ ፫ ቀበሌ ፲፪ የቤት ቁጥር ፪፻፳፱ የሆኑት ከየካቲት ፳፱ ቀን እስከ መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም በከባድ ሕመም ሲሰቃዩ እንደቆዩና በዚሁ ደብር ደህንነት እንዳገኙ ከዚህ እንደሚከተለው ቃላ



አቶ ንዋይ ገብረ ማርያም

ቸውን ሰጥተዋል ፣ ከላይ በተጠቀሰው ወርና ዓመተ ምህረት ሰውነቴን በድን አድርጎ ሽንቴንም ከልክሎ ልሳኔን ዘግቶ የያዘኝን የልክፍት በሽታ ለመከላከል በመጀመሪያ ድርሳነ ሚካኤል አስደግሜ ተጠመቅሁ ነገር ግን ሳይሻለኝ በመቅረቱ ጓደኛዬ የሆኑት አቶ ሸዋዬ ተክሌና አቶ ቡሽራ ሌንጮ በባለቤቴ በወይዘሮ አበበች ደምሴ አማካይነት ከሕዝቡ ጋር እየተረዳዱ በቃሬዛ ወደዚሁ ቤተ ክርስቲያን እያመላለሱኝ የቅዱስ ወንጌሉና የጻድቁ ተክለ ሃይማኖት ገድል የተነበበትን ጸበሉን ስጠመቅ በ፳፬ ሰዓት ልሳኔ በሚገባ ሊፈታልኝ ችሎአል ሽንቴንም እንደዚሁ በ፳፬ ሰዓት እንደልብ ለመሽናት ችያለሁ ።

በመጨረሻም ሰውነቴ በሙሉ እንደ ቀድሞው ሙሉ ጤንነት አግኝቶ ከያዘኝ ኃይለኛ ቁራኛ ተላቅቄ እለሁ ተፈውሻለሁ ስል ትክክለኛ የእምነት ቃሌን በመስጠት ልዑል



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር መሐሪ አምላክ መሆኑንና ታላቁ ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አማላጅ አባት መሆናቸውን በትክክል እመሰክራለሁ በማለት በደስታና በምስጋና ተናግረዋል ።

፭ኛ/ ወ/ት ሠይናት ሙሉጌታ ዕድሜዋ ፲፱ ዓመት ሲሆን የ፲፩ኛ ክፍል ተማሪ ናት ሠናይት በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም አንድ የማላውቀው ሕመም ለከፈኝ ትላለች ሲጀምረኝ ሆዴን እየነፋ መራ መድ ይከለክለኝ ነበር በ፲፱፻፷፱ ዓ/ም ደግሞ እግሬና እጄን እያሳበጠ በተለይም ከግራታፋዬን ሕመሙ እየገባመራመድ ከልከሉኝ በጣም ያሰቃየኝ ነበር ውሎ አድሮም ልቤን እያደከመ ያለሁበትን እስከስት ደርሼ ነበር ።

ይህ ሁሉ ሊደርስብኝ የቻለውም ጓደኛዬ የእጅ ሥራዬን ወስዳ ለጠንቋይና ሊቃልቻበማቀራኘትና በማስተሳሰር ሕገ ወጥ ሥራ ስለፈጸመችብኝ እጄ እንዳይሠራና እንዳይንቀሳቀስ ፈዞ ቀርቶ ነበር ይሁንና በሕክምና ብዙ ከደከምሑ በኋላ ምንም ሊሻለኝ ስላልቻለእግዚ አብሔር ለምሕረት ጠርቶኝ ኖሮ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ወደ ዚሁደብር ማለትደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በቤተ ሰቦቼ እማካኝነት መጥቼ ሲያጠምቁኝ የተቀራኘኝ እርኩስ በሽታ በላዩ ላይ ሆኖ እንደ ጮኸና እንደለፈለፈ ተነግሮኛል ሆኖም በዚሁ ሥፍራ ጠበሉን እየ ተጠመቅሁ ለሁለት ወራት ከቆየሁ በኋላ ሐኪሞች (ዶክተሮች) ያቃታቸውን በሽታ በእግዚአብሔር ቸርነት በጻድቁ በአቡነ ተክለ ሃይማኖት አማላጅነት ልላቀቅ በቅቻለሁ ።

ስለዚህ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሁሉ ከማንኛውም ሥቃይና መከራ እግዚአብሔርን በማመን ደህንነት እንደሚገኝ እያረጋገጥሁ እደኔ በጽኑ በሽታ የተያዝችሁ እንዳላችሁም ወደ ልዩ ልዩ ከቱ ወደ ሆኑት አምልኮቶች መሄድን ትታችሁ ወደዚሁ ቅዱስ ሥፍራ መጥታችሁ ከበሽታችሁ ተላቀቁ ብየ እግረ መንገዱን አሳስባችኋለሁ በማለት የምስክርነት ቃሏን ሰጠች ።

፮ኛ/ ወ/ት እቴቱ ተፈራ በማላውቀው በሽታ ተለክፌ ለአምስት ዓመታት ያህል ስሰቃይ ከቆየሁ በኋላ በዚሁ ሥፍራ ጠበል ተጠምቄ ተገላግያለሁ እያለች ትመሰክራለች እቷቱ በሽታው እንዴት እንደ



ወ/ት ሠናይት ሙሉጌታ

ጀመራት ለቀረበላት መጠይቅ ስት መልስ በመጀመሪያ በት/ቤት ስማር ሳለሁ አይኔን ጋረደኝ ቀጥሎም በየሜዳው ያስጮኸኛል ስሄድ‧ምበመየንገዱ ይጥለኛል ከዚያም የተነሣ ትምህርቴን ከ፺ኛ ክፍል አቋርጬ በ፲፺ ዓመቴ ከተወለድሁበት ቦታ ለቅቄ ወደ ድሬዳዋ ሄድሁኝ በዚያው ለአንድ ዓመት ያህል ከሰው ጋር ስቀመጥ ከማንም ሰው እያጋጨ እያነጫነጨ ስምምነት እሳጥቶች ስቀመጥ እንደ ገናደግሞ አእምሮየን ለሁለት ወር ያህል ሰውሮኝ በጽኑ ሥቃይ ቆየሁ በመጨረሻ የምኖርባቸው ሰዎች በሽታሽ ምን እንደሆነ አይታወቅምና ወደ ሀገርሽ ተመለሽ አሉኝ ነገሩበጣም ስላስጨነቀኝ ለሰው አማክርሁኝ አዲስ አበባ ብትሄጅ በተክለ ሃይማኖት ቤተክርስቲያን ፈዋሽ የሆነ ጠበል አለ ተጠምቀሽ ለመዳን ትችያለሽ አሉኝ እኔም ከዚያተነሥቼ ወደ አዲስ አበባ መጣሁ ለእናቴ ስንኳ ሳላማክርና ሳልነግር ወደዚሁ ደብር መጥቼ ፲፭ ቀን ያህል ብጠመቅ በዱር በገደልና በሽንተረር እያዞረ ከሰው ጋር እያጋጨና በየመንገዱ እየጣለ ለአምስት ዓመታት ያህል በጽኑ ደዌ ይዞኝ የነበረ በሽታ ለቆኝአሁን ነፃ ሆኜ ሙሉጤ ነንትም አግኝቼ ከቤተ ሰቦቼ ጋር ተገናኝቼ እነሆ ያቋረጥሁትን ትምህርት ቀጥያለሁ ፣ ስለዚህ ሕሙማን ሁሉ ወደዚሁ ደብር እየመጣችሁ ከበሽታችሁ እንድትላቀቁ እየጠቆምሁ መዳን የሚገኘው በክርስቶስ እንጂ በማንም እንዳይደለ በእውነት እየመሰከርሁ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ከእንግዲህ ወዲህ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው ? በማለት ጽኑ እምነቴን አረጋግጣለሁ በማለት ከእግዚአብሔርና ከጻድቁ ከተክለ ሃይማኖት ያገኘችውን ፍቅር በዚሁ አጋጣሚ ገልጻለች ።

አንባብያን ሆይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሲያስተምር ብዙ ልዩ ልዩ ደዌ የያዛቸው ሰዎች ነበሩ ከበሽታቸው ለመላቀቅሁሉን ወደሚችል ወደ መድኃኒታችን ክርስቶስ እየመጡ የተፈወሱት ግን ጥቂቶች ናቸው ከተፈወሱት መካከልም አንዳንዶቹ ብቻ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሕያው የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ መሆኑን ያስፍርሐት ሲመሰክሩለት አብዛኛዎቹ ግን ደህንነት አግኝተው ከኅብረተ ሰቡ መካከል ከተቀላቀሉ በኋላ አንድ ቀን ስኳን አል መሰከሩለትም ነበር ለምሳሌ ጌታችን ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለሙሄድ ሲነሣ በሰማርያ መካከል አለፈ ወደ አንዲት መንደር እንደ ደረሰም አሥር ለምጻሞች ቁመው አገኘ እነርሱም እየጮሁ ኢየሱስ ሆይ አቤቱ ማረን አሉት እርሱም ሂዱ ራሳችሁንም ለካህን አሳዩ (አስመርምሩ) አላቸውና ሲሄዱ በመንገድ ከለምጻቸው ነጹ ነገር ግን



ወ/ት እቴቱ ተፈራ

ተከታዩን በ፲፰ኛው ገጽ ይመልከቱ



# የበዓላትና የአጽዋማት መግለጫ ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለዘመናት አቈጣጠር እንዲሁም ስለበዓላትና አጽዋማት አወጣጥ በምትመራበት ባሕረ ሐሳብ መሠረት አቈጣጠሩ (አስተሳሰቡ በዓመት በዓመቱ ከፍና ዝቅ (ውጣ ውረድ) ያለበት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ምክንያት ተከታዮቿምእመናንችግር እንዳይገጥማቸው በማለት የበዓላትንና የአጽዋማትን መግለጫበየጊዜው በዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ በካላንደርም እያዘጋጀች ማቅረቧ ይታወሳል ። ዛሬም በዚያው መሠረት እንደተለመደው የሺ ፱፻፸፫ ዓመተ ምሕረትን የበዓላትና የአጽዋማት መግለጫ ለምእመናን እነሆ በሚከተለው አኳኋን አቅርበናል ።

## ዘመነ ማቴዎስ ወንጌላዊ

ያዘመን መለወጫ ቀን ሐሙስ
ዓመተ ዓለም ፯ ሺህ ፱፻፸፫
ዓመተ ምሕረት ፩ሺህ ፱፻፸፫
አበቅቴ ፳፭
መጥቅዕ ፭
የዕለት ተውሳክ ፬
ጾመ ነነዌ የካቲት ፱
ዓቢይ ጾም የካቲት ፳፫
ደብረ ዘይት መጋቢት ፳
ሆሣዕና ሚያዝያ ፲፩
ስቅለት » ፲፮
ትንሣኤ » ፲፰
ርክበ ካህናት ግንቦት ፲፪
ዕርገት » ፳፯

ጰራቅሊጦስ ሰኔ ፯ ፣ ጾመ ሐዋርያት ሰኔ ፰ ፣ ዐርብ ረቡዕ ሰኔ ፲ መሆኑን ጭምር ለምእመናን እየገለጽን በዚህ አጋጣሚ አምላክ ሰላም እንኳን ለዘመነ ማቴዎስ አደረሳችሁ በማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መልካም ምኞቷን ትገልጻለች።ከዚህም ሌላ በመጠኑም ቢሆን ዐበይት በዓላትና ንዑሳን በዓላት የሚውሉበትን ቀጥሎ ያለውን ለአንባብያን ምእመናን እንገልጻለን ዐቢያን በዓላት ትስብዕት መጋቢት ፳፱ ፣ ልደት ታኅሣሥ ፳፱ ፣ በ፬ኛው ዓመት (፳፰) ጥምቀት ጥር ፲፩ ቀን ፣ ደብረ ታቦር ነሐሴ ፲፫ ቀን፣ ሆሣዕና፣ ስቅለት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት፣ ጰራቅሊጦስ ናቸው ።

### ተሰዓቱ ንዑሳን በዓላት

መስቀል መስከረም ፲፯ ቀን፣ስብከት፣ብርሃን ኖላዊ ጌና ታኅሣሥ ፳፰ ቀን፣ግዝረት ጥር ፮ ቀን፣ በዓለ ስምዖን የካቲት ፰፣ደብረ ዘይት፣መስቀል መጋቢት ፲፣ መስቀልና መስቀል አንድ ወገን ቢሉ ፱ነኛ ቃና ዘገሊላ ነው ።

### የ፲፪ቱ ሐዋርያት በዓላት

መስከረም ፩ በርተሎሜዎስ፣ ጥቅምት ፲፪ ቀን ማቴዎስ ኅዳር ፲፰ ቀን፣ ፊልጶስ ታኅሣሥ ፬ ቀን እንድርያስ ጥር ፬ ቀን ወልደ ነጎድጓድ ዮሐንስ ፣ የካቲት ፲ ቀን ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ፣ መጋቢት ፰ ቀን ማትያስ፣ ሚያዝያ ፲፯ ቀን ያዕቆብ ወዘብዴዎስ ፣ ግንቦት ፳፮ ቀን ቶማስ፣ ሐምሌ ፪ ቀን ታዴዎስ፣ሐምሌ ፭ ቀን ጴጥሮስ ወጳውሎስ፣ ሐምሌ ፲ ቀን ናትናኤል ነው ።

ታኅሣሥ በባተ በ፩ ተንኤልያስ ሰኞ ቀን ቢውል በ፯ኛው ቀን ስብከት ይሆናል ።

| | |
|---|---|
| ማክሰኞ ቢውል | በ፲፫ኛው ቀን |
| ሮብ | በ፲፪ኛው ቀን |
| ሐሙስ | በ፲፩ኛው ቀን |
| ዐርብ | በ፲ኛው ቀን |
| ቅዳሜ | በ፱ኛው ቀን |
| እሑድ | በ፰ኛው ቀን ይውላል። |

ከ፯ ወደ ፮ አይወርድም፣ ከ፲፫ ወደ አ፲፬ አይወጣም ።

### ስለጳጉሜን

ስድስተኛዪቱ ጳጉሜን ከዐውደ አበቅቴ ገብታ አለመቆጠሯ ስለም ነው ቢሉ ወንጌ ላውያን በሰዓት በኬክሮስ ከ፬ ቢከፍሏትእንጂ እንደአምስተኛዪቱ ጳጉሜን ለእያንዳንዱወንጌላውያን ስለማትደርሳቸው ከዐውደ አበቅቴ አለመቈጠሯ ስለዚህ ነው

# መዝሙረ አውደ ዓመት ።

ከይቁም ግዛው

ልጁም አዋቂውም ሰላም ጤና ለብሰህ

ከዘመን፣እዘመን እንኳን አደረሰህ
ዘመን ሲለዋወጥ ባመት ባመቱነው
የሰው ጠባይ ለውጡ በየሰዓቱ ነው

ግሪክ ነበር የሚል ቴዎስ እግዚአ ብሔን

ማቴዎስ ይለዋል ዛሬ በኛ ዘመን ፤
አርፈን ነበር አምና ባለፈውዘመን ፤
እንግዲህ አመጡት አበቅቴያቸውን
አበቅቴ እንደወተት አልቦነበር አ ምና

ዛሬ ለኛ ሰጠን አብዮትና ጠና
አይጽፍሞይ ደርሶ ,ታሪክ ጸሐፊው

ታሪክ እኮ እሚጻፍ ባዲስ ዘመንነው
ይመስለኝ ነበረ ፍጹም ገዳማዊ
ዮሐንስ መጥምቁ ፍጹም ዘመናዊ
ራሱን የማይጥል ከሰው ሁሉ በላይ
ዮሐንስ ብቻ ነው ሁል ጊዜ ዘመናይ
ጥቅመራራ ስትዘፍን ስትደንስ ሰሎሜ ።
ዮሐንስ መጥምቁ ያላረጀ በድሜ
ከአንገቱ ወረደ እያለ ገዳሜ
የዮሐንስ አንገት ሲለካ ሲመተር
አንዱ ለመሠረት አንዱ ሆነጠፈር
ዋገምቱ ጠፋብኝ እያለ ሲያለቅስ
ብላችሁ ንገሩት ዋገምቷል ሔሮድስ
ዮሐንስ ሲያስተምር እስካለምዛርቻ
አስቸግሮት ቀረ የሔሮድስ ጋብቻ
ሔሮድስ ዮሐንስን እንዴትይመ ነው
የዮሐንስ ፍቅሩ ካንገት በላይ ነው
ያዘመን ሽማኔው ድሩን እያደራ
ለአብዮት ኩታ ጥበቡን ሲሠራ
ቅቤስ የለም አትበል ላውደ ዓመታቸው



www.ethiopianorthodox.org

ለወይዛዝርት ያህል አለ ቀባቸው
አጋተች ላማችን ከዕለት ዕለት
ሐሰትም እንዳይደል እዩት ያንንግት
ሁሉ እየተነሣ አይቡን አይቡን
ታዲያ ማን ይጠጣው አጓት አጓቱን
የኢትዮጵያ ጀግና ጥንትምአንድላይ
እንደንጹሕ ውተት ርጎ አይደ
ለምወይ
ጀበና ያልሞላው ከረምቱን ነበር
አሁን በጋንሞልቷል ቡናና ስኳር
ይታረዱ ይቈፈር ጋራው ጉባውም
ቢሆን እንደ ጋራው ጉቦ አይጠ
ቅመንም
ያገራችን ጉባ ጠፋን እያላችሁ
ባለታሪክ ልጆች እዩት ያውጉ
ባችሁ

ሌላው በእግር ነው አዜብ በበ
ቅሎ ነሽ
አገርሽ ስትገቢ በግርማ ቀደመሽ
አዜብ ታሪክሽን እየመረመረው
ልብ አድርጎ አስቦ ምኒልክ ዐጤነው
ኢትዮጵያም እንግዲህ ወርቅነው
ግብርሽ
ደግሞም በበለጠ ዕንቍም ለጣጣሽ
ዘመን ሲያዩ ነው አንድ ላይ
እኔም ፈለገኝ ዘመን አይ
ሌላ እኮ መስሎኝ ሲቀድስ
ለካ ራሱ ነው ዮሐንስ
ሰይፉን ተውና ለነጌሮድስ
ጽናና መስቀል ይዘህ ቀድስ
ሰይፉን ይዞነው ጌሮድስ
የሚቀድሰው ከመቅደሰ
ዮሐንስ አንተን ማንደርሶብህ
ሰይፍ እየጠባህ ተቀማጥለህ
በቤተ መንግሥትነው ያደግህ
ለምን ሰሰተ ለቍርስ
ያ ካልበላ ሖሮድስ
የመጥምቁ ራስ መርዶውን
ታረጂ መጣሽ አሁኑን
ታሪክ ከፈለግሽ እንድትኮሪ
የመጥምቁ ራስ የማትፈሪ

ሒጂ ወደዚያ ላይ ብረሪ
በዓል ጠብቆ ባለዛሩ
በግ ያርዳል እኮ በየዱሩ
ዘመን ሲለውጥ ለበዓል
ደግሞ ቢጋጣ ይሆናል
ቃልቻው ብታርድ ሙክት ሰንጋ
እኔ ግደለኝ ላንተ ሥጋ
አያድርም እኮ ሳይቀምስ
ያለሙክት ዛር ፈረስ
ብርሃኑ ከኛ ይታያል
ደግሞ ዛሩ ቤት ደምብዟል
በወጣቷ አድሮ መሳሳት
ያስግዳታል ለጣእት
ካህኑ ይህን ስታስተምር
ተውጣጣ ከቤት እንዳትቀር
አንዳንድ ሰዎች አይነኩት
የጣዖቱን መሥዋዕት
እየሠው ቤት
ዛሩ አፋሽከው ይኸው
አው ሊያ አሰኘው
ዛሩም ፋሽኮ ይዟል
ቢኖውን ይመጣል
ሰው ለራሱ ቅራሪ አጥቶ
ጅን ይጋብዛል ተሳስቶ
ሥጋ አምላክ ሳለ መድኃኒት
እንደዚህ አርጎ መሳሳት



ይቁም ግዛው ።
ሌት ናተኛ ቢለው ለእንቅልፍ ነው
ሥራውን ሊያስፈታ ቀናተኛ አለው
ተቀናብሮ መብላት ልጆች ወደዳ
ችሁ
ታዲያ እስኪቀናበር ታገሡ እባካ
ችሁ
አዜብ ተቀበይ እየተደሰትሽ
ሕዝቡ ልኮልሻል ዕንቍ ለጣጣሽ
ታዲያ ምን ይልክ ነው ለታላቅ
ክብርሽ
በኢትዮጵያ ብቻ አዜብ ሳትረጋ
ይስገድላት እንጂ የሰሎሞን ዜጋ
ለጥቂት ቀንም ቢሆን ተቀምጣ
ለች ባልጋ

የጽዮን ካህናት ሲጠባበቋት
አዜብስ ደረሰች ለዳዊት ምራት
ከሀገሯ አዜብ በክብር እንደሄደች
በክብር ተነሥታ ወዳገሯ ገባች

# በአሥመራ ከተማ በክፍለ ሀገር

ከ፳፩ኛው ገጽ የዞረ

ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በተላኩት
መምህራን ።
፩ኛ/ ስለስብከተ ወንጌል መሠረ
ታዊ ዓላማና ዘዴ በቀሲስ ዘውዴ
ታችበሌ ፤
፪ኛ/ በጕብዝናህ ወራት ፈጣሪህን
አስብ ፣ በአቶ ገብረ ክርስቶስ ኃይለ
ማርያም ።
፫ኛ/ ስለቃለ ዓዋዲ አጭር ማገለጫ
በቀሲስ ኃይለ ልውል ወ/ገሪማ
፬ኛ/ ስለቃለ ዓዋዲ ጥናት » »
፭ኛ/ ስለወጣቶች በሰንበት ት/ቤት
መደራጀት በመሪጌታ ፀሐይ ብር
ሃኑ ትምህርት ተሰጥቶአል ። የት
ምህርቱ አሰጣጥ ከተፈጸመ በኋ
ላም ጉባኤው በአራቱ ወንጌላው
ያን ምሳሌ በአራት ቡድን ተከ
ፋፍሎ ስለቤተ ክርስቲያናችን ጠቅ
ላላ አቋም ጉዳይ ወቅታዊና እንገ
ብጋቢ በሆኑት ነገሮች ላይ ትኩ
ረት በመስጠት ዓበይት ነጥቦችን
እያነሣ ለችግሮችም መፍትሔ ናቸ
ው ተብሎ የሚታመንባቸውን በመ
ጠቀም እያንዳንዱ የዕረፍቱን
ሰዓት እንኳ ሳይቀር በመሠዋት
ስፋትና ጥልቀት ባለው ሁኔታ
ሲወያይ ሰንብቶአል ።
በመጨረሻም ስለሰበካ ጉባኤ
ማቋቋምና የቃለ ዓዋዲን ደንብ
አፈጻጸም ፣ ስለካህናት ጠቅላላ
ሁኔታ ፣ ስለስብከተ ወንጌልና ሰባ
ክያን ፣ ስለወጣቶችና የወጣቶች
ማኅበራትን በሚመለከቱ ጉዳዮች
ተወያይቶ ባለ አሥራ ሰባት ነጥ
ብ ውሳኔ በማሳለፍ ነሐሴ ፳፮
ቀን ፲፱፻፷፪ ዓ/ም ጠቅላላ ስብ
ሰባውን ፈጽሞአል ።



# እ ና ስ ተ ዋ ው ቃ ች ሁ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋ
ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪካውያን
ቅርሶችዋንና ስነ ጽሑፎችዋን ጥን
ታውያን የብራና መጻሕፍትንና አል
ባሳትን ፣ እንደሻማና እንደ ጧፍ ፣
እንደዕጣንና እንደ ወይን የመሳ
ሰሉትን ምርቶችና እንደ ጽላትና
እንደ መስቀል ያሉትን የተቀደሱ
ቅርጻቅርጾች በጠቅላላ ልዩ ልዩ
ንዋያተ ቅድሳትን እያዘጋጀ የሚ
ያቀርብ የንዋየ ቅድሳት ፣ የብራና
መጻሕፍት ቅርሳቅርስ ጥናትና
ዕቅድ ዋና መምሪያ ተቋቁሟል ፣
ይኸውም መምሪያ የሚከተለውን
ፕላንና ዕቅድ ስለአቀረበ በፕ
ላኑና በዕቅዱ መሠረት ሐሳቡ ተግ
ባራዊ እንዲሆንለት ማዕዶት መጽ
ሔት እየተመኘ ፕላኑንና ዕቅዱን
እነሆ ከዚህ ቀጥሎ አቅርቦአል ።

ፕ ላ ን ፤

አርእስት ፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ
ሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፤ የንዋየ
ቅድሳት የብራና መጻሕፍት ቅር
ሳቅርስ ጥናትና ዕቅድ ዋና መም
ሪያ ፤ የሚከተሉት ዋና ዋና ክፍ
ሎች ይኖሩታል ።

ክ ፍ ል ፩

ሀ/ የንዋየ ቅድሳት የአልባሳት
ማደራጃ ዋና ክፍል ፤

፩/ የቤተ ክርስቲያን የካህናትል
ብሰ ተክህና
፪/ የጳጳሳት ልብሰ ተክህኖና ቆብ
፫/ የመነኮሳት የካህናት ቀሚስ
ፈረጅያና ቆብ
፬/ የተለያየ የሙካሽ ጥልፍ ሥራ
፭/ ምንጣፍ የሥጋጃ ሥራ
፮/ በተለያየ ዓይነት ጥበብ የሸማ
ሥራ

ክ ፍ ል ፪

ለ/ የእንጨትና የብረታ ብረት ቅ
ርጻቅርጽ ዋና ክፍል፣

፩/ ታቦተ ሕግ የጽላት ሥራ
፪/ የተለያዩ ዓይነቶች የመስቀል
ሥራ
፫/ የቤተ አምላክ መንበሮችሥራ
፬/ በሐረግ የተቀረፀ የቤተ ክርስ
ቲያን መዝጊያና መስኮት
፭/ የልብሰ ተክህኖ ማስቀመጫ
የተለያዩ ዘመናዊ ቁም ሳጥኖች
፮/ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሕ
ዝብ ማረፊያ የተለያዩ ወን
በሮች



አባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስ የመምሪያው
ኃላፊና የፕላኑ አዘጋጅ

ክ ፍ ል ፫

ሐ/ የሻማና የጥዋፍ ዋና ክፍል

፩/ ለቤተ ክርስቲያንና ለሕዝብ
ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ሻማ
ዎች መሥራት
፪/ ለቤተ ክርስቲያንና ለሕዝብ
ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ ጥዋ
ፎች መሥራት
፫/ ለቤተ አምላክና ለሕዝብ የሚ
ስማማ የዕጣን ቅመማ ሥራ

ክ ፍ ል ፬

መ/ የወፍጮና የዳቦ መጋገሪያ
ዋና ክፍል

፩/ ለቤተ ክርስቲያን የሚሆን ን
ጹህ ስንዴ ማደራጃ
፪/ ለካህናት ማሰልጠኛ የሚሆን
ዳቦ መሥሪያ
፫/ በቤተ ክርስቲያን ስም ለሚ
ያድጉ ሕፃናት ዳቦ ማቅረብያ

www.ethiopianorthodox.org